# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 263 ግንቦት 23 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# ‹‹ኢትዮጵያ ቁልፍ መሠረተ ልማቶቿን ለመገንባት ዘላቂ ወዳጆችን ትፈልጋለች››

- አቶ ተመስገን ጥሩነህ
የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ:- ኢትዮጵያ ቁልፍ መሠረተ ልማቶቿን ለመገንባት ዘላቂ ተባባሪ ወዳጆችን ትፈልጋለች ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ ተናገሩ።

አቶ ተመስገን ጥሩነህ "ኢትዮጵያን እንገንባ!" በሚል መሪ ሃሳብ በሚሊኒየም አዳራሽ የተዘጋጀውን ሁለተኛውን ዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን ዐውደ ርዕይ (ቢግ 5 ኮንስትራክት ኢትዮጵያ) ትናንትና መርቀው ከፍተዋል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን በመክፈቻ መድረኩ ላይ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ቁልፍ መሰረተ ልማቶቿን ለመገንባት፣ በተመጣጣኝ ወጪ መኖሪያ ቤቶችን ለዜጎች ለማቅረብ እንዲሁም የተሻሉ የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም ዘላቂ ተባባሪ ወዳጆችን ትፈልጋለች።

ሁለተኛው የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ለኮንስትራክሽን ዘርፉ ሰፊ ትኩረት ሰጥቷል ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ከሀገራዊ ጥቅል ምርት 21 በመቶ ድርሻ እንዳለው አስረድተዋል።

የባቡር ፣ የመንገዶችና የተለያዩ መሠረተ ልማት ግንባታ፣ የኃይል አቅርቦትና መገልገያዎች ግንባታ፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮችና ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ምስረታ ትኩረት ከተሰጣቸው መካከል መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

በኮንስትራክሽን ዘርፉ የሚከናወኑ ኢንቨስትመንቶች በፍጥነት በማደግ ላይ ያለውን የከተሞችን ዕድገት ለመምራት እንዲሁም የኢኮኖሚ ዕድገቱን ለመደገፍ

« ኢትዮጵያ ቁልፍ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# የምክክሩ ተሳታፊዎች የውክልናውን ክብደት በመረዳት በቅን ልቦና መወያየት አለባቸው

- ዛሬ በአዲስ አበባ የባለድርሻ አካላት ውይይት ይጀመራል

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- የምክክሩ ተሳታፊዎች የውክልናውን ክብደት በመረዳት በቅን ልቦና መወያየት እንዳለባቸው የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ገለጸ። ዛሬ የባለድርሻ አካላት ውይይት እንደሚጀመርም ተጠቁሟል።

የምክክር ኮሚሽኑ ኮሚሽነር ብሌን ገብረመድህን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአዲስ አበባ የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ እየተሳተፉ ያሉ ተሳታፊዎች ከተጽዕኖ ነጻ ሆነው በቅን ልቦና መሳተፍ አለባቸው።

ተሳታፊዎቹ ወገንተኛ ሳይሆኑ ትርጉም ባለው መልኩ መሳተፍ አለባቸው ያሉት ኮሚሽነሯ፤ በውይይቱ የምፈልገውን ሃሳብ ብቻ ልስማ ሳይሉና የሰው ሃሳብ ሳያጣጥሉ መሳተፍ አለባቸው ብለዋል።

ምክክሩ ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ መሆኑን ገልጸው፤ ተሳታፊዎቹ መጀመሪያ በአነስተኛ ቡድን ለ10 ተወያይተው በመግባባት ቀጥለው

የምክክሩ ተሳታፊዎች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ጃፋር በድሩ

# የኢትዮጵያን የባህር ጥያቄ ጉዳይ አጀንዳ ያሳደረገ እንቅስቃሴ ብዙ ርቀት እንደማይጓዝ ተገለጸ

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን የባህር ተደራሽነት አጀንዳው የማያደርግ የኢኮኖሚና የጸጥታ ውይይት በቀጣናው ዘላቂ ልማትና በሰላም ማረጋገጥ እንደማያስችል የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያን የባህር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ከሦስት ሚሊዮን በላይ የግብርና ማሽነሪዎች ወደ ሀገር ገቡ

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ሦስት ሚሊዮን 385 ሺህ 137 የግብርና ማሽነሪዎች ከቀረጥና ከታክስ ነጻ ወደ ሀገር እንዲገቡ መደረጉን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ሜካናይዜሽን ሥራ አስፈጻሚ ተወካይ እሸቱ ሁንዴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ሁለት ሚሊዮን 532 ሺህ 454 የድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎች እና 852 ሺህ 683 ለቅድመ ምርት የሚያገለግሉ የግብርና ሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች ከቀረጥና ከታክስ ነጻ ወደ ሀገር እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

አቶ እሸቱ ሁለት ሚሊዮን 210 ሺህ 327 ዘመናዊ የእህል ማከማቻዎች ፣ ሦስት ሺህ 675 ትራክተሮች ፣ 652 ሺህ 92 የመርጫ መሳሪያዎች ፣ 196 ሺህ 916 የውሃ ፓምፖች ፣ 217 ሺህ 58 መውቂያዎች ወደ ሀገር

ከሦስት ሚሊዮን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# ለ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና

## የተማሪዎች ዝግጅት

**ማርቆስ በላይ**



የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናን አልፎ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን መቀላቀል የተማሪዎች ህልም ነው። እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ የፈተና አሰጣጥ ሥርዓቱ ለኩረጃና ስርቆት የተጋለጠ እንደነበር ይነገራል። በዚህም በርካቶች ያልዘሩትን ሲያጭዱ ተስተውሏል።

በፈተና ስርቆት ሳቢያ ለሚደገመው ፈተና ሀገር ላልተገባ ወጪ ተዳርጋለች። በተማሪዎች ላይ ይዞት የሚመጣው ሥነ ልቦናዊ ጫና ቀላል የሚባል አልነበረም። በመሆኑም ባለፉት ዓመታት የትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የተለያዩ እርምጃዎች እየወሰደ ይገኛል።

በዋናነት የፈተና ስርቆትንና ማጭበርበርን ለማስቀረት በኤሌክትሮኒክስ መስጠት እስከሚጀመር የሁለተኛ ደረጃ ብሔራዊ መልቀቂያ ፈተና በዩኒቨርሲቲ እንዲሰጥ አድርጓል። ይህም ተማሪዎች ትምህርት በጥናትና በታታሪነት የሚገኝ መሆኑን አውቀው በርትተው መማርና ማጥናት እንዳለባቸው የሚያስችል መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል።

ታዲያ ትምህርት ሚኒስቴር ፈተናውን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከመስጠት ባለፈ የ2016 ዓ.ም 12ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና በተመረጡ ከተሞች በኦንላይን እንደሚሰጥ አሳውቋል። ለፈተናውም ኮምፒውተሮች፣ ላፕቶፖችና ታብሌቶችን ጨምሮ ሌሎች ግብአቶችን የማሟላት ሥራ በስፋት እየሠራ ይገኛል።

ተማሪ ማዕዶት ብርሃኑ የዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 12ኛ ክፍል ተማሪ ነው። እሱ እንደሚለው፤ ትምህርት ቤቱ የተለያዩ ለፈተና የሚያስፈልጉ የድጋፍ ትምህርት በመስጠት፣ ጥያቄዎችን በመሥራት፣ የሥነ ልቦና ዝግጅትና ስለ ኦንላይ ፈተና አወሳሰድ የግንዛቤ ማስጨበጫ እየተሰጣቸው እንደሚገኝ ይናገራል።

በቤተ መጽሐፍት ቀደም ሲል የነበሩ የመማሪያ መጽሐፍትን ጨምሮ ፈተናዎችን እና አስፈላጊ ግብዓቶች መቅረባቸውን በመጥቀስ፤ የተሻለ ውጤት ለማምጣት ጥያቄዎችን መሥራትና መርጃ መጽሐፍትን በማንበብ ለፈተናው የሥነ ልቦና ዝግጅት እያደረገ እንደሚገኝ ያስረዳል።

ሌላዋ በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ትምህርት ቤት የ12ኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው ሜላት ደረጀ እንደምትገልጸው፤ በዘንድሮ በኦላይን ለሚሰጠው የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ መልቀቂ ፈተና ትምህርት ቤታቸው ኦንላይ ፈተና አወሳሰድ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ እየሰጣቸው መሆኑን ነግራናለች። እሷና ጓደኞቿም በዌብሳይቶች አማካኝነት ልምምድ እያደረጉ ነው።

ትምህርት ቤቱ ከዓመቱ መጀመሪያ ጀምሮ ተጨማሪ የትምህርት ክፍለ ጊዜዎችን በመስጠትና ቤተ መጽሐፍትን በማዘጋጀት ድጋፍ እያደረገላቸው እንደሚገኝ ትናገራለች።

‹‹መምህራን ጥያቄዎችን በመሥራት፣ ያለፉትን ትምህርት ተመልሶ በማስተማር፣ የመለማመጃ ጥያቄዎች በማዘጋጀት ይረዱናል›› ስትል ገልጻለች።

እንደ ተፈታኝ ተማሪ የሚጠበቅባትን ዝግጅት እያደረገች እንደምትገኝና ከጓደኞቿ ጋር በጋራና በቤተ መጽሐፍት በማጥናት፣ ጥያቄዎችን በመሥራት፣ ለፈተና የቀረውን ጊዜ በአግባቡ ለመጠቀም እየጣሩ እንደሚገኙ ታብራራለች።

‹‹አንድ ሰዓትም ቢሆን ያለ አግባብ መባከን የለበትም፤ ምክንያቱም ይሄ ብሔራዊ ፈተና ነው›› የምትለው ተማሪዋ፤ የትምህርት ቤቱ መምህራንም ተማሪዎቹ ያልገባቸውን ጥያቄዎችን በማስረዳት ተገቢውን ድጋፍ እያደረጉ እንደሚገኙ ታመለክታለች።

ዘንድሮ በኦንይን የሚሰጠው ፈተና የመጀመሪያ እንደመሆኑ ዝግጅት በማድረግ ላይ እንደምትገኝ ገልጻ፤በፈተና ወቅት የመብራት፣ኢንተርኔት፣የተለያዩ ችግሮች እንዳያጋጥሙ ሥጋት እንዳደረባትም ትልጻለች።

ዘንድሮ በኦንላይ ለሚሰጠው የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ የመልቀቂያ ፈተና ተማሪዎች በብቃት መውሰድ እንዲችሉ አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ላይ እንደሚገኝ የሚገልጹት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወይዘሮ ቀለመወርቅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ኤፍሬም አይተንፍሱ ናቸው።

ርዕሰ መምህሩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዘንድሮው በኦንላይ ለሚሰጠው የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ከዓመቱ መጀመሪያ ጀምሮ ተማሪዎችን የማዘጋጀት ሥራ እየተሠራ ይገኛል።

ትምህርት ቤቱ በዘንድሮ ዓመት 185 የማህበራዊና 145 የተፈጥሮ ሳይንስ በድምሩ 330 ተማሪዎችን ለማስፈተን መዘጋጀቱን ይገልጻሉ። በዚህም ተማሪዎች የኦንላይ ፈተና አሠራር ሂደትን እንዲገነዘቡ በአይሲቲ መምህራን አማካኝነት ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ ይጠቅሳሉ። በተለይም በባለፈው ዓመት የተሰጡ ፈተናዎችን በኦንላይን እንዲለማመዱ መደረጉን ይናገራሉ።

ለተማሪዎች የማጣቀሻ መጽሐፍትን የማቅረብ፣ የሥነ-ልቦና ድጋፍ፣ የኮምፒውተር አቅም ማሳደግ እና የትምህርት ይዘት ሽፋን እየተሰጠ ነው። መምህራንም ተማሪዎችን ለፈተና ብቁ ለማድረግ የሚያስችሉ ድጋፎችን እያደረጉ እንደሚገኙ ያስረዳሉ።

ትምህርት ቤቱ ለፈተናው የሚያስፈልጉ የኮምፒውተር፣ የኢንተርኔትና የመብራት አቅምን የማሳደግና ግብዓት ለማሟላት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየሠራ መሆኑንም ይጠቁማሉ።

# በሀዋሳ ከተማ ወንጀልን በመከላከሉ ሥራ ኅብረተሰቡ እንዲሳተፍ በመደረጉ ወንጀል ቀንሷል

## - በከተማው ከ470 በላይ የሺሻ ማስጨሻ ቁሳቁሶች እንዲወገዱ ተደርጓል

**አምሳሉ ፈስቀ**

አዲስ አበባ፡- የከተማው ማሕበረሰብ ወንጀልን በመከላከል ሥራ ከጸጥታው መዋቅር ጋር በባለቤትነት እንዲሳተፍ በመደረጉ ወንጀል እንዲቀንስ መደረጉን የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ መምሪያ አስታወቀ፡፡

የከተማ አስተዳደሩ ፖሊስ መምሪያ ኃላፊ ምክትል ኢንስፔክተር መልካሙ አየለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ከማሕበረሰቡ ጋር በመቀናጀት የተጠናከረ የቀንና የማታ ቅኝት እየተደረገ ነው፡፡ በዚህም የከተማው ማሕበረሰብ ወንጀልን በመከላከል ሥራ ከጸጥታው መዋቅር ጋር በባለቤትነት እንዲሳተፍ በመደረጉ ወንጀል እንዲቀንስ ተደርጓል፡፡

በከተማው ከዚህ ቀደም አልፎ አልፎ በባለሁለት ጎማ ሞተር ሳይክል የታገዘ ንጥቂያ እና ሌሎችም ወንጀሎች ይፈጸሙ እንደነበር ያወሱት ምክትል ኢንስፔክተሩ፤ ከተማውን ከየትኛውም የወንጀል ስጋት ነጻ ለማድረግ ከማሕበረሰቡና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ እየሠራ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

በተለይም በባለሁለት ጎማ ሞተር ሳይክል የታገዘ የንጥቂያ ወንጀልን ለመከላከል በተከናወኑ ሥራዎች በተለያዩ አካባቢዎች ላይ ከ163 በላይ የሚሆኑ ተጠርጣሪዎች ለዝርፊያ ከሚጠቀሟቸው ሞተር ሳይክሎች ጋር ተይዘዋል ያሉት ምክትል ኢንስፔክተር መልካሙ፤የተሰረቁ ዕቃዎችን ከሌቦች እጅ የሚረከቡ ተጠርጣሪዎችም ጭምር ተይዘው በሕግ እንዲጠየቁና ውሳኔ እንዲሰጥባቸው መደረጉን ተናግረዋል፡፡

ሀዋሳ ከተማን ከየትኛውም የወንጀል ስጋት ነጻ እንዲሆን በተከናወኑ ዘርፈ ብዙ ተግባራት ከተማው በአሁኑ ወቅት ከየትኛውም ጊዜ በላይ ሰላሙ እንዲረጋገጥ መቻሉን ገልጸዋል፡፡

በከተማው ወንጀል ይፈጸምባቸዋል ተብሎ በተለዩ አካባቢዎች ላይ ማሕበረሰቡ በራሱ ባደረገው ትብብር በዚህ ዓመት ከ40 በላይ የማሕበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት መገንባታቸውንም በማስታወስ፡፡

በተለይም የወጣቱን የሕብረተሰብ ክፍል ኢኮኖሚያዊ፡ ማሕበራዊ፡ ስነልቦናዊና ዕሴቶችን የሚጎዱና ለወንጀል ተግባራት እንዲነሳሱ የሚያደርጉ አደንዛዥ ዕጾችን ከመከላከል ረገድም ውጤታማ ስራ መሰራቱን ገልጸው፤ በከተማው አልፎ አልፎ ጫት መቃሚያ ቤቶች፡ ሺሻ የሚጨስባቸው ቦታዎችና ምሽት ጭፈራ ቤቶች አካባቢ ሕጋዊነትን በተከተለ መንገድ በተደረገው ኦፕሬሽን ከ470 በላይ የሺሻ ዕቃዎች ተይዘው ማሕበረሰቡ ባለበት እንዲወገዱ መደረጉንም ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡

ይህ ብቻም ሳይሆን ወጣቱን ለአልባሌ ሱሶች የሚያጋልጡና የሥራ መንፈስ እንዳይኖራቸው የሚያደርጉ ሁኔታዎች የመከላከሉ ሥራም ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡

በከተማው በአሁኑ ወቅት ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖራቸው ከሌላ አካባቢ በመጣው ፈቃድ የሚሠሩ በተለይም ሸርቹዋልና ቤቲንግ የሚባሉ ውርርድ ቤቶች እንዳሉ የጠቆሙት ምክትል ኢንስፔክተር መልካሙ፤ እነዚህ ውርርድ ቤቶች በተለይም በትምህርትና መኖሪያ ቤቶች አካባቢ ሕጻናት ያለዕድሜያቸው ወደዚህ ተግባር የሚገቡበትና ወጣቶችም የሚሳተፉበት ሁኔታ በመፈጠሩ በዘርፉ የተሰማሩ አካላትና ድርጅቶች ከሚመለከታቸው አካላት ሕጋዊነትን በተከተለ መንገድ ብቻ ዕውቅና እስኪያገኙ መታገዳቸውንም አስታውቀዋል፡፡

የከተማ ነዋሪ የራሱንና የአካባቢውን ሰላምና ጸጥታን በማስጠበቅ ረገድ በባለቤትነት ከጸጥታው መዋቅር ጋር በቅንጅት ይሠራል ያሉት የከተማው ፖሊስ መምሪያ ኃላፊ፤ የጸጥታ ሥራውን ዘመናዊ ከማድረግ አንጻር በከተማ አስተዳደሩ በጥናት በተለዩ ቦታዎች፣ በመንግሥት፣ በግል እና በንግድ ተቋማት አካባቢ የተተከሉ ዘመናዊ ካሜራዎችም ለወንጀል መከላከል ሥራው ትልቅ አስተዋጽኦ እያበረከቱ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

በዚህም ከተማው ሰላማዊና ዜጎች ያለስጋት የሚንቀሳቀሱበት፤ ለሥራ፣ ለኑሮ እና ለመዝናናት ተመራጭ እየሆነ መምጣቱንም አስረድተዋል፡፡

# ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ አደጋዎችን ለመከላከል ባለድርሻ አካላት በትብብር ሊሠሩ ይገባል

## - በመዲናዋ ከ36 ሺህ በላይ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭ ናቸው

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ምክንያት የሚከሰቱ አደጋዎችን ለመከላከል ባለድርሻ አካላት በትብብር ሊሠሩ እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አደጋና ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ፡፡ ኮሚሽኑ በመዲናዋ የአደጋ ስጋት ተጋላጭነት ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትናትናው ዕለት ውይይት አካሂዷል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አደጋና ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽነር ፍቅሬ ግዛው በወቅቱ እንደገለጹት፤ መጪው ጊዜ የክረምት ወቅት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሊያጋጥም የሚችል አደጋን ለመከላከል ባለድርሻ አካላት በትብብር ሊሠሩ ይገባል።

የአደጋ ተጋላጭ ሥፍራዎችን በጥናት በመለየት ዓለም አቀፍ መስፈርትን የተከተለ የአደጋ ስጋት መከላከል እንዲኖር እየተሠራ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ ይህም የአደጋ ተጋላጭነትን ለይቶ መሥራት ውጤታማ ያደርጋል ብለዋል፡፡

ኮሚሽኑ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ያስጠናቸው ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፤ በአዲስ አበባ ከተማ ለእሳት፣ ለጎርፍ፣ ለመሬት መንሸራተትና መሰል አደጋዎች ተጋላጭ የሆኑ 505 ቦታዎች መለየቱን አስታውቋል፡፡

የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ግንዛቤ ስርጸት ቡድን መሪ አቶ መኩሪያው ግዛው በበኩላቸው፤ በ2016 ዓ.ም በተደረገ ጥናት በመዲናዋ 218 ቦታዎች ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭ መሆናቸውን ገልጸው፤ ሊያጋጥም የሚችለውን አደጋ ለመቅረፍ በትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ መኩሪያው ገለጻ፤ ከ36 ሺህ በላይ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭ መሆናቸውን ገልጸው፤ኮሚሽኑ አደጋውን ለመከላከል በሚሠራው ሥራ ኅብረተሰቡ ንቁ ተሳታፊ ሊሆን ይገባል ብለዋል። በተለይም ጉለሌ፣ አቃቂና ኮልፌ ክፍለ ከተሞች ትልቁን ቁጥር እንደሚይዙ ተገልጿል፡፡

ኮሚሽኑ በተለያየ ወቅት የአደጋ ተጋላጭነት ጥናት በማድረግ፣ መረጃ በማደራጀትና ለሚመለከታቸው ተቋማት በማስተላለፍ መፍትሔ እንዲሰጥ ክትትልና ድጋፍ ሲያደርግ መቆየቱን አስረድተዋል፡፡

በመዲናዋ በሁሉም ክፍለ ከተማ አፋጣኝ የማቅለያ እርምጃ የሚያስፈልጋቸው 135 ከፍተኛ የጎርፍ ተጋላጭ ቦታዎች መኖራቸውን ጠቁመው፤የቅድመ መከላከል ሥራው ተጀምሯል ብለዋል፡፡

የከተማዋ የመልካ ምድር አቀማመጥና የዜጎች አሰፋፈር ለሚያጋጥሙ የጎርፍም ሆነ የእሳት አደጋ መጨመር ዋነኛ ምክንያት መሆኑን በጥናቱ መረጋገጡን ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን የድልድይ አስተዳደር ቡድን መሪ አቶ መላኩ ታደሰ በበኩላቸው፤ ባለስልጣኑ ክረምት ከመግባቱ ቀደም ብሎ በጀርመን አደባባይ፣ ማንጎ ጨፌ ሃና ማርያም አካባቢ፣ ሰፈራ አካባቢ እንዲሁም ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭ የሆኑ 56 ቦታዎች ላይ የቅድመ መከላከል ሥራ እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

በከተማው የተጀመረው የኮሪደር ልማት ሥራም በነዋሪው ህይወትና ንብረት ላይ ሊያጋጥም የሚችለውን የጎርፍ አደጋ ለመከላከል እንደሚያግዝ ተገልጿል።

በወንዝ ዳርቻና በተጋላጭ ቦታ ያሉ ሰዎች ከአደጋው ቦታ አስቀድመው እንዲነሱ ሲጠየቁ ያለመተባበር፣ ሥራው የሚጠይቀውን በጀት፣ ዲዛይን፣ ግብዓትና የሰው ኃይል በወቅቱ በትኩረት ያለማዘጋጀት ሥራው ውጤታማ እንዳይሆን ተግዳሮት መሆኑ ተመላክቷል፡፡

# ከበጋ መስኖ ስንዴ ከ99 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ተሰበሰበ

**ታደሠ ብናልፈው**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> ከ2016 የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እስካሁን ከ99 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት መሰብሰቡን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የግብርና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈፃሚ አቶ ከበደ ላቀው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016 የስንዴ ምርትን ምርታማነትን ለማሳደግ እየተሠራ ባለው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እስከ ግንቦት 18 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ከ99 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ተሰብስቧል፡፡

በግብርናውን ዘርፍ የስንዴን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በበጋ መስኖ፣ በበልግና በመኸር ወቅቶች በስፋት የማምረት ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ከበደ፤ በ2016 የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት 120 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት ለማግኘት ታቅዶ እስካሁን ድረስ 99 ሚሊዮን 173 ሺህ 601 ኩንታል ምርት ተሰብስቧል ብለዋል፡፡

በሀገሪቱ በሁሉም ክልሎች በ2016 በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር መሸፈኑን አውስተው፤ ከዚህም 120 ሚሊዮን ኩንታል



የስንዴ ምርት ይገኛል ተብሎ እንደሚጠበቅ ተናግረዋል፡፡

በበጋ መስኖ ስንዴ በዘር ከተሸፈነው ሶስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ ሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን የሚሆነውን መሰብሰብ ተችሏል ያሉት ሥራ አስፈፃሚው፤ ከተሰበሰበው ሁለት ሚሊዮን 700 ሺህ ሄክታር መሬት የበጋ መስኖ ስንዴ ውስጥ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በሰው ኃይል እና 700 ሺህ ሄክታሩ መሬቱ ደግሞ በኮባይነር የተሰበሰበ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

የስንዴ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ትልቅ ሚና እንዳለው ገልጸው፤ የበጋ መስኖ ለምቶ የደረሰውን ቀሪ ሰብል በወቅቱ ሰብስቦ በማጠናቀቅ የታቀደውን 120 ሚሊዮን ኩንታል ምርት የማሳካት እቅድን ተግባራዊ ለማድረግ ሰፊ ርብርብ እየተደረገ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ከኢትዮጵያ የአየር ትንበያ ወቅታዊ የአየር መረጃ በማሰባሰብ አርሶ አደሩ ምርቱን በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲሰበስብ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው፤ይህም አሠራር በምርቱ ላይ ምንም አይነት ጉዳት ሳይደርስበት በጥራት እንዲሰበሰብ ያስቻለ ነው ብለዋል፡፡

ቀሪውን የበጋ መስኖ ስንዴ በጥራት ለመሰብሰብ ከኢትዮጵያ ሚትሮዎሎጂ ኢንስቲትዩት ጋር በቅንጅት እየሰራን ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በበጋ መስኖ ስንዴ ለምቶ የነበረውንና የተሰበሰበን መሬት ዳግም ምርት እንዲሰጥ ለማድረግ ለበልግ ልማት የማዋል ሥራ እየተከናወነ ነው ያሉት የሕዝብ ግንኙነት ሥራ አስፈፃሚው፤ ከበልግ ልማት ከፍተኛ ምርት ለማግኘት የተጠናከረ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ጠቁመዋል፡፡



# የለሚ ሲሚንቶ ፋብሪካ በመጪዎቹ ሁለት ወራት ወደ ማምረት ይገባል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> የለሚ ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ በቀጣይ ሁለት ወራት ወደ ማምረት እንደሚገባ ተገለጸ።

የማዕድን ሚኒስትሩ ኢንጅነር ሀብታሙ ተገኘ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን የበጀት ዓመቱን የዘጠኝ ወር ሪፖርት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንት ባቀረቡበት ወቅት እንደተናገሩት፤ በሀገሪቱ በሲሚንቶ ምርት፣ አቅርቦትና ግብይት ከፍተቶች ይታያሉ፡፡ ይህም ምርት እጥረት የሚፈጥረው ክፍተት በርካታ ተያያዥ ችግሮችንም የሚያስከትል ነው። ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል።

የለሚ ሲሚንቶ ፋብሪካ በቀጣዮቹ ሁለት ወራት ወደ ማምረት እንደሚገባ ገልጸው፤ ይህም አሁን ያለውን የሀገሪቱን የሲሚንቶ ምርት አቅርቦት እስከ 40 በመቶ የሚሸፍን እንደሚሆን ተናግረዋል።

ፋብሪካው የመጀመሪያውን ምእራፍ ሲያጠናቅቅ ሦስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ቶን፤ እንዲሁም ሁለተኛው ምእራፍ ሲጠናቀቅ አጠቃላይ በዓመት ስድስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ የሚያመርት መሆኑንም ገልጸዋል።

በተመሳሳይ በረንታ የሲሚንቶ ፕሮጀክት አሁን በአካባቢው ያሉ ችግሮች ተፈትተው ወደ ማምረት ሲገባ በቀን ሰባት ሺህ በላይ ቶን ሲሚንት እንደሚያመርት አመልክተው፤ ሙሉ ለሙሉ ወደ ማምረት ሲገባም 23 ሺ 400 ቶን በቀን እንደሚያመርት ይጠበቃል ብለዋል። እነዚህ ውጤቶች በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አበረታች አፈጻጸም ካስመዘገበባቸው መስኮች መካከል ይገኙበታል።

የሲሚንቶ ምርት አቅርቦትን ለማሻሻል በተለያዩ ጊዜያት አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያጋጥሟቸውን የጸጥታና ተያያዥ ችግሮች በቅርበት በመፍታት የተለያዩ ውጤቶች ማስመዝገብ ተችሏል። በዚህም ለመሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ወደ ሥራ እንዲገባ መደረጉን አውስተዋል።

ባለፉት ዘጠኝ ወራት በሀገር አቀፍ ደረጃ አምስት ነጥብ 42 ሚሊዮን ቶን ለማምረት መቻሉን ገልጸው፤ ይህም ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ22 በመቶ ብልጫ እንዳለው ተናግረዋል፡፡ በዚህም ከዚህ ቀደም በገበያ ላይ ተከስቶ የነበረውን የሲሚንቶ አቅርቦት እጥረት በተወሰነ ደረጃ ለማረጋጋት መቻሉን አመልክተዋል።

በሌላ በኩል ተኪ ማእድናትን በተመለከተም የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች በዋናነትም የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ከውጪ የሚያስገቡትን የከሰል ድንጋይ የመተካት ሥራ እየተሠራ ይገኛል። ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለድንጋይ ከሰል ተጠቃሚ ሲሚንቶ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከአጠቃላይ ፍጆታቸው 64 በመቶ ለመሸፈን መቻሉንም ጠቁመዋል።

# ምክክሩ በግጭት ተጎጂ ለሆኑት ሴቶች እፎይታን ይሰጣል

**መዓዛ ማሞ**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> ሀገራዊ ምክክሩ ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም በማምጣት የግጭት ዋነኛ ተጎጂ ለሆኑት ሴቶች እፎይታን እንደሚሰጥ የምክክሩ ሴት ተሳታፊዎች ገለጹ።


በአዲስ አበባ የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ በሴቶች የማህበረሰብ ዘርፍ ተሳታፊ የሆኑት ወይዘሮ የአለምዘውድ ጥላሁን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሀገራዊ ምክክሩ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያለውን አለመግባባት በውይይት በመፍታት ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ያመጣል።



የአለምዘውድ ጥላሁን

ግጭቶች ሲከሰቱ ሴቶች ሕፃናት ልጆቻቸውን ይዘው በመፈናቀል ለከፍተኛ ችግር እንደሚጋለጡ ጠቁመው፤ ምክክሩ በውይይት ችግሮች እንዲፈቱ በማድረግ የሴቶችን ስቃይ በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል ብለዋል።

እንደ ሀገር ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ በሀገራዊ ምክክሩ በነጻነት እና በግልጽ በመወያየት መፍትሔ ማበጀት አለብን ያሉት ወይዘሮ የአለምዘውድ፤ በውጤቱ ሁሉም በሰላም የሚኖርባት ሀገር መፍጠር እንደሚቻል አመላክተዋል።



ጌጤነሽ በልሁ

ሃሳባቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያጋሩት የምክክሩ ተሳታፊ ወይዘሮ አጃኢባ መሀመድ በበኩላቸው እንደሚሉት፤ ሀገራዊ ምክክሩ ለዜጎች ምቹና ሰላማዊ ሀገር የሚፈጥር ነው።

በሚፈጠሩ አለመግባባቶች ሴቶች የችግሩ ዋነኛ ተጠቂዎች መሆናቸውን አውስተው፤ሀገራዊ ምክክሩ በኢትዮጵያ የሚታዩትን አለመግባባቶች በምክክር እና በውይይት እንዲፈቱ በማድረግ ለሴቶች ምቹ ሀገር እንደሚፈጠር ገልጸዋል።

ሴት እናት እንዲሁም ሚስት በመሆኗ በማህበረሰቡ ዘንድ ተሰሚነት አላት የሚሉት ወይዘሮ አጃኢባ፤ ሴት ተሳታፊዎች ምክክሩ በስኬት እንዲጠናቀቅ እና ሁሉም ወደ ሰላም እንዲመጣ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጠይቀዋል።



አጃኢባ መሀመድ

ወይዘሮ ጌጤነሽ በልሁ የተባሉት የምክክሩ ተሳታፊ በበኩላቸው ሃሳባቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሀገራዊ ምክክሩ የሴቶችን ትልቅ ችግር የሚፈታ ነው። ምክንያቱም ሴቶች የሰላም እጦት የትዳር አጋሮቻቸውን እና ልጆቻቸውን የሚያሳጣቸው ነው፡፡ እንዲሁም ለስደት በመጋለጥ ከፍተኛ ችግር ያጋጥማቸዋል።

ሀገራዊ ምክክሩ አለመግባባቶችን በውይይት በመፍታት ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ወሳኝ መሆኑን አመላክተው፤ ምክክሩ የሚያስገኘው ሰላም ለሴቶች እፎይታን የሚሠጥ መሆኑን ገልጸዋል።

ሀገር ሰላም ካልሆነች ሴቶች በይበልጥ ለችግር እንደሚጋለጡ የተናገሩት ወይዘሮ ጌጤነሽ፤ በምክክሩ የሚሳተፉ ሴቶች መግባባት ለመፍጠር እየተካሄደ በሚገኘው ውይይት ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የመፍትሔ አካል እንዲሆኑ ጠይቀዋል።

# በትግራይ ክልል የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ተፈታኞች ዝግጅታቸውን እያጠናቀቁ ነው

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና የሚወስዱ 53 ሺህ በላይ ተማሪዎች አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲያደርጉ ድጋፍ እየተደረገ ነው ሲል የክልሉ ትምህርት ጥራት ኤጀንሲ አስታወቀ፡፡

የክልሉ ትምህርት ጥራት ኤጀንሲ ዳይሬክተር ዶክተር ታደሰ ካሕሳይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤በሀገር አቀፍ ደረጃ የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ሐምሌ 3 ቀን 2016 ዓ.ም ይሰጣል፡፡ በክልሉ ለሁሉም ተፈታኞች ለ12ኛ ብሔራዊ ፈተና እንዲዘጋጁ ለማድረግ የሚያስችል የቲቶሪያል ትምህርት እየሰጠ ነው፡፡

በክልሉ የሚሰጠው ፈተና በሁለት መንገድ መከፈሉን ገልጸው፤አንደኛ ኮድ እና ሁለተኛ ኮድ በመባል የሚታወቁ ተፈታኞች እንደሚኖሩ ተናግረዋል፡፡እነዚህም በጦርነቱ ምክንያት ሳይፈተኑ የቀሩ እና በአሁኑ የትምህርት ዘመን ተምረው የሚፈተኑ ናቸው ብለዋል፡፡

በክልሉ ሃምሳ ሦስት ሺህ የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ተፈታኞች መመዝገባቸውን የገለጹ ሲሆን፤ምዝገባው በዲጂታል ሲስተም መደረጉን አውስተዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜም የክልሉ ትምህርት ቢሮ ለሁሉም ተፈታኞች የቲቶሪያል ትምህርት እየሰጠ ነው ብለዋል፡፡

የመፈተኛ ቦታ በተመለከተ አብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች በጦርነቱ ምክንያት በመጎዳታቸው፤ተፈታኞች በክልሉ በሚገኙ የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች በኦንላይን ለመፈተን ከተማሪዎች እና ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመነጋገር ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ነው የተናገሩት፡፡

በተመሳሳይ በክልሉ የሚሰጠው የስምንተኛ ክፍል ማጠቃለያ ፈተና መዳረሱን የገለጹ ሲሆን፤ 123 ሺህ ተፈታኞች በሁለት ባች ተከፍለው ይፈተናሉ ብለዋል፡፡

የተፈታኞች ምዝገባ ለመጀመሪያ ጊዜ በሶፍትዌር መዘጋጀቱን በመጥቀስ፤እርማቱም በዚሁ ሶፍትዌር እንደሚከናወን እና ፈተናው በህትመት ዝግጅት ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

ክልሉ በዓመት ሁለት ጊዜ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች መፈተኑን የጠቀሱ ሲሆን፤ከዚህ ቀደም ያልተፈተኑ ስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ታህሳስ ወር 2016 ዓ.ም ፈተና መሰጠቱን አውስተው፤ የፈተናው እርማት በአስር ቀናት ውስጥ መጠናቀቁን ተናግረዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በመማር ላይ ለሚገኙ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ከሰኔ 11 እስከ 13 ቀን 2016 ዓ.ም እንደሚሰጥም ጠቁመዋል፡፡

# የምክክሩ ተሳታፊዎች የውክልናውን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

እንደ ቡድንና እንደ ኀብረተሰብ ክፍል እንደሚግባቡ ገልጸዋል።

የምክክሩ ሂደት አንድ ደረጃ ከፍ ማለቱን የተናገሩት ኮሚሽነር ብሌን፤ በጋራ የማንግባባቸው ጉዳዮች እንደ ከተማ አስተዳደር የተወሰኑ የተዘረዘሩ ጉዳዮች እንደሚኖሩና ሁሉም አካላት አንድ ላይ በመገኘታቸው የሚፈቱ ጉዳዮች ይኖራሉ ብለዋል።

የባለድርሻ አካላት መድረክ ዛሬ እንደሚጀመር ተናግረው፤ በመድረኩ አዲስ አበባ ላይ ያሉ ሲቪክ ማህበራት፣የሃይማኖት ተቋማት፣የፖለቲካ ፓርቲዎች፣የአካል ጉዳተኞች ማህበራት፣የሴቶች ማህበራት፣ ወጣቶች፣የቀድሞ ሠራዊት፣ ሠራተኞች፣ አሠሪዎች፣የመንግሥት ሠራተኞች፣የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች፣የአዲስ አበባ ምክር ቤት፣የአዲስ አበባ ሥራ አስፈጻሚ፣የተለያዩ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎች ስብስብ እንደሚሳተፉበት ተናግረዋል።

በባለድርሻ አካላት ውይይት እስከ አንድ ሺህ የሚደርሱ ተሳታፊዎች እንደሚሳተፉ አመላክተው፤ በዛሬው መድረክ ገለጻ እንደሚደረግ፣ ነገ ቅዳሜ የመከፈቻ መርሀ ግብር ተደርጎ በቀጣዩ ቀን በቡድን እና በጋራ እንደሚወያዩ ጠቁመዋል።

እየተወያዩ ላሉ ተሳታፊዎች አጀንዳ ያልሰጡ ሰዎች በአካል ተገኝተው፣ በፖስታ እንዲሁም በኢሜይል አጀንዳቸውን ለኮሚሽኑ መላክ እንደሚችሉ ገልጸው፤ ኮሚሽኑ ተቀብሎ እንደሚያስተናግድ አመላክተዋል፡፡

የሚዲያ ተቋማትም የምክክር ሂደቱን ሕዝብ እንዲረዳው በማድረግ የጀመሩትን ሥራ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጠይቀዋል፡፡

ኮሚሽኑ ቃል አቀባይ አቶ ጥበቡ ታደሰ በበኩላቸው፤ የምክክሩ አጀንዳ ማሰባሰብ ሥራ በአዲስ አበባ መጀመሩን አስታውሰው፤ በመዲናዋ በሚገኙ 119 ወረዳዎች ተወካዮች ውይይት ማድረጋቸውን ጠቁመዋል።

ለውይይት ምቹ በሆኑ ሁኔታ የዕጩዎች ጥቆማ አድርገዋል። ውይይቶቹ ስኬታማ ነበሩ። ዛሬ ደግሞ የተጠቆሙ ዕጩዎችን ወደውክልና የማምጣትና የተሰባሰቡ አጀንዳዎችን የመለየት ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

በሌላ መድረክ ደግሞ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በቀጣይ በሚኖሩ የምክክሩ ሂደት ላይ ገለጻና ማብራሪያ ይደረግላቸዋል።



ብሴን ገብረመድህን

# ከሦስት ሚሊዮን ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

መግባታቸውን ገልጸው፤ በተጨማሪም የተለያዩ ኮምባይሮች ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባበሪያዎች ፣ ማበጠሪያ እና መፈልፈያዎች በብዛት ገዝተዋል ብለዋል፡፡

ማሽነሪዎቹ ከገቡም በኋላ የግብርና መካናይዜሽን ማሽነሪዎችን የአጠቃቀም ስልጠና የሚሰጡ ባለሙያዎችን በማዘጋጀት በተለይም አፋር እና በሱማሌ ክልሎች ላይ የተለያዩ የአጠቃቀም ስልጠናዎች መሰጠታቸውን የገለጹት አቶ እሸቱ፤ በተጨማሪም በተለያዩ ከተሞች ለ238 ሞዴል አርሶ አደሮች ስልጠናው ተደራሽ መደረጉን ተናግረዋል፡፡

ማሽነሪዎችን ከማስገባት ጎን ለጎን የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት መስጫ ዘጠኝ ማዕከላትን በማቋቋም የማጠናከር ሥራ ተከናውኗል ያሉት አቶ እሸቱ፤ በተጨማሪም በተቋቋሙት የአገልግሎት ማዕከላት ለሚያገለግሉ 78 ባለሙያዎች የአራት ዙር ስልጠና መሰጠቱን ገልጸዋል፡፡

አሁን በዋናነት ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ ያለው የግብርና መካናይዜሽን ግብአቶች ከገቡ በኋላ በትንሹ እስከ አስር ዓመት ማገልገል እንዲችሉ ለአርሶ አደሩ ስልጠና በመስጠት ላይ መሆኑን የገለጹት አቶ እሸቱ፤ ደረጃና ሥርዓተ ትምህርት ለማሻሻል እንዲሁም የግብርና ሜካይዜሽን ቴክኖሎጂ ኦፐሬሽን እና ጥገና ባለሙያዎችን በማሰልጠንም የሙያ ደረጃ እንዲሻሻል እየተሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

# የኢትዮጵያን የባህር ጥያቄ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ሁለተኛው የቀይ ባህር ውይይት ከቀጣናው ሀገራት ጋር በትናንትናው ዕለት ተካሂዷል። በውይይቱ ወቅት የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ጃፋር በድሩ ለጋዜጠኞች እንደገለጹት፤ በቀይ ባህር ላይ ለሚነሱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጉዳዮች ኢትዮጵያ እንደሚመለከታት የሚያሳስብ ውይይት ነው። የኢትዮጵያ የባህር ተደራሽነት ማግኘትን አጀንዳው የማያደርግ በቀጣናው የሚደረግ የኢኮኖሚና የጸጥታ ውይይት በቀጣናው ዘላቂ ልማትንና ሰላምን ማረጋገጥ አይችልም ብለዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ከኢትዮጵያ ጋር ታሪካዊ ቁርኝ ያላቸው ሀገራት የቀይ ባህር ካውንስል በማቋቋም ኢትዮጵያን የማግለል ሥራ ይሠራሉ። በቀይ ባህር ደህንነትና የኢኮኖሚ ልማት ዙሪያ ውይይቶችን ያደርጋሉ። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያን ያገለለ ማንኛውም እንቅስቃሴ በቀጣናው ዘላቂ ሰላምና ልማት አያመጣም።

የኢትዮጵያን የባህር ጥያቄ ጉዳይ አጀንዳ ያላደረገ እንቅስቃሴ ብዙ ርቀት አይጓዝም ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ውይይቱ ኢትዮጵያ በቀጣናው ሰላም፣ልማትና ዘላቂ ደህንነት ላይ የራሷን አስተዋጽኦ የምታደርግ ሀገር መሆኗን እንዲታወቅ እንደሚረዳም አመልክተዋል።

በቀይ ባህር ዙሪያ የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ እድገትና የሕዝብ ብዛትን በመገንዘብ በቀጣናው የኢትዮጵያን ፍላጎቶችና ስጋቶች እንዲሁም የወደፊት ህልሞችን ማዕከል ያደረገ ውይይት መደረግ እንዳለበት አቶ ጃፋር አሳስበዋል።

መሰል ውይይቶች ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ዙሪያ የምትገለለ ሀገር አለመሆኗን ለማሳየት ይረዳል ያሉት አቶ ጃፋር፤ ኢትዮጵያ በታሪክ አጋጣሚ የባህር በር አልባ ብትሆንም ከቀይ ባህር ጋር ታሪካዊ ቁርኝት አላት ነው ያሉት።

መሠረታዊ ህልውናዋና ታሪኳ የተመሠረተው በቀይ ባህር ዙሪያ ላይ ነው። ኢትዮጵያን የማግለል ሂደት የረጅም ጊዜ ሴራ አካል መሆኑን አመልክተው፤ በአሁኑ ጊዜ በመንግሥት እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች ኢትዮጵያ የቀይ ባህር ኃይል ሆና የምትመለስበትን አግባብ ወይም ስልት ለመቀየስ የሚረዳ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ፣ ብሔራዊ ደህንነቷና ዓለም አቀፍ የኢንተርኔት ዝርጋታዋ ሙሉ ለሙሉ በቀይ ባህር ላይ በሚደረጉ መስተጋብሮች የተንጠለጠለ ነው። ከዚህ አንጻር የቀይ ባህር ጉዳይ ለኢትዮጵያ የህልውና ጉዳይ በመሆኑ ኢትዮጵያን ማግለል ተገቢ አይደለም፤ ለቀጣናውም ጠቃሚ አይደለም።

ከላይኛው የቀይ ባህር ሀገራት እስከ ሶማሌ ላንድ ያሉ ሀገራት ተወካዮችን፣ አሰላሳዮችን፣ ምሁራንንና አምባሳደሮችን በመጋበዝ የሚደረጉ ውይይቶች ኢትዮጵያ የቀይ ባህር ሀገር መሆኗን የሚያጸና ነው። ውይይቱ በተጨማሪም ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር ጋር የተሳሰረ ህልውናና የወደፊት እጣፈንታ ያላት ሀገር መሆኗን ለማሳየት የሚጠቅም ነው ብለዋል።

የቀይ ባህር ጉዳይ አጀንዳ ከመሆኑ በፊት የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ስትራቴጂ አውጥቶ ሲሠራ መቆየቱ ተገልጿል።

# ‹‹ኢትዮጵያ ቁልፍ መሠረተ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

አስፈላጊ መሆናቸውን አብራርተዋል።

አቶ ተመስገን እንደጠቆሙት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የኮንስትራክሽን ዘርፉ በመሠረተ ልማት ግንባታ፣ በሥራ ዕድል ፈጠራን በማበረታታት ከፍተኛ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ሆኗል።

በመሠረተ ልማት ግንባታው የኢትዮጵያን የመንገድ ግንባታ ሽፋን አሁን ካለበት ከ166 ሺህ ኪሎ ሜትር ወደ 246 ሺህ ኪሎ ሜትር ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን አመላክተው፤ በኮንስትራክሽን ዘርፉ በዓመት ለሁለት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን ገልጸዋል።

ዘርፉ ያለውን አቅም ለማጎልበት መንግሥት የተለያዩ የፖሊሲና የታክስ ማበረታቻዎች ማድረጉን አስታውሰዋል፤ በግንባታው ዘርፍ ኢንቨስትመንት በመሳብና ልማቱን በመደገፍ ረገድ የሚከናወነው ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ በተዘጋጀው ዓለም አቀፉ ዐውደ ርዕዩ የመጪው ዘመን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መልክ እያስያዙ ያሉ የዘርፉ መሪዎች፣ አምራቾች፣ የሃሳብ አመንጪዎችና ባለሙያዎችን እየተሳተፉ መሆኑን አስረድተዋል።

የኮንስትራክሽን ዐውደ ርዕዩ አዳዲስ ትብብሮችን የሚፈጥርና የሁለትዮሽ ጠቀሜታን የሚያጎለብት እንዲሁም በዘርፉ ዘላቂ ወዳጆችን መፍጠር የሚያስችል መሆኑን አመላክተዋል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ በበኩላቸው፤ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በርካታ ባለድርሻዎችን የሚያሳትፍና ሰፊ ሀብት የሚጠይቅ ነው፤ ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ ካደጉ ሀገራት ጋር በትብብር መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

ዐውደ ርዕዩ በሌሎች ሀገራት ያለውን የቴክኖሎጂ አቅምና ልምድ በማምጣት የተሻለ ሥራ ለማከናወን ይረዳል ብለዋል።

የዐውደ ርዕዩ በኢትዮጵያ መዘጋጀት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ለማነቃቃት፣ የዘርፉን ዋነኛ ተዋንያኖች እርስ በእርስ ለማስተዋወቅና አብሮ የመሥራት ባህልን ለማዳበር እንደሚያግዝ ጠቁመዋል።

ከዐውደ ርዕዩ ጎን ለጎን የኮንስትራክኙን ዘርፉን በዕውቀት በምርምርና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መደገፍ የሚያስችሉ አውደ ጥናቶች እንደሚካሄዱ አመላክተዋል።

በዐውደ ርዕዩ መክፈቻ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ የትምህርት ሚኒስትር ብርሃኑ ነጋ (ፕ/ር)፣ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪሃት ካሚልና የተለያዩ ሚኒስትሮች ተገኝተዋል።

በሚሊኒየም አዳራሽ እየተካሄደ በሚገኘው ዐውደ ርዕይ ከቱርክ፣ ከቻይና፣ ከጣልያን፣ ከኬንያና ከተለያዩ ሀገራት እየተሳተፉ ነው፤ ዐውደ ርዕዩም ነገ ይጠናቀቃል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ፍላጎቶችን ማጣጣም የሚያስችል አዲስ የፖለቲካ አስተሳሰብ ለመፍጠር

በአንድ ሀገር ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ልዩነቶችንም ሆነ እነሱን ተከትሎ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ ተነጋግሮ መፍታት የሚችል ሀገራዊ ማህበራዊ የአስተሳሰብ መሠረት መፍጠር ያስፈልጋል። ለዚህም ደግሞ እንደ ሀገር ያሉ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እሴቶችን ደጋግሞ በአግባቡ መገምገም፤ በአዎንታዊ ሆነ በአሉታዊ መልኩ በማህበረሰቡ ሁለንተናዊ ፍላጎት ላይ የሚፈጥሩትን ጫና አጥርቶ ማወቅ ያስፈልጋል ።

በተለይም እኛ ኢትዮጵያውያን እንደ ሀገር አሁን ባለንበት የለውጥ ወቅት፤ ለውጡ እንደ ቀደሙት ዘመናት ለውጦች ብዙ ያልተገባ ዋጋ አስከፍሎን የተፈለገውን ውጤት ሳያስገኝ እንዳይመክን፤ ከሁሉም በላይ ልዩነቶችን በመነጋገር መፍታት፤ ዘላቂ ሀገራዊ ሰላም ማስፈን የሚያስችል አዲስ ማህበረሰባዊ የፖለቲካ ባህል ፣ ለዚህ የሚሆን ሁለንተናዊ ዝግጁነት መፍጠር ይኖርብናል።

ለእኛ ያለንበትን ድህነት እና ኋላ ቀርነት አሸንፎ መውጣት እንደ ሀገር የህልውና ጉዳይ ከሆነብን ዓመታት ተቆጥረዋል፤ ይህንን የህልውና አደጋ የምንሻገረው ዘመኑን በሚዋጅ የልማት እሳቤ ነው። ለዚህ ደግሞ ሰላም ወሳኙ ጉዳይ ይሆናል። ዘላቂ ሰላም መፍጠር የምንችለው ደግሞ የተለያዩ ፍላጎቶችን አጣጥሞ የሚሄድ ማህበረሰባዊ የአስተሳሰብ መሠረት መገንባት ስንችል ነው ።

ያለ ሰላም የበለጸገች ሀገር መፍጠር ቀርቶ ነገን ተስፋ አድርጎ መቆም አይቻልም። ለዚህ በየዘመኑ ከተፈጠሩ የለውጥ ንቅናቄዎች ማግስት እንደ ሀገር ያጋጠሙን ፈተናዎች እና ፈተናዎቹን ለመሻገር የከፈልናቸው ያልተገቡ ዋጋዎችን ማሰብ ይበቃል። ይህም ለለውጥ እሳቤዎች ስኬት ሰላም የቱን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያመላክታል።

በዘመናት መካከል እንደ ጥላ እየተከተለ ትውልዶችን ብዙ ዋጋ እያስከፈለ ያለውን ሀገራዊ የሰላም እጦት ለዘለቄታው መፍታት አሁን የሁሉንም ዜጋ የነቃ ተሳትፎ የሚጠይቅ ሆኗል፤ አዲስ የአስተሳሰብ ባህል መፍጠር እና ማዳበር ፤ ለዚህ የሚሆን ከትናንት የተማረ አእምሮ መፍጠርም ትኩረት ሰጥተን ልንሰራው የሚገባን ዋነኛ የቤት ሥራችን መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል።

አሁን ያለንበት ወቅት ከመቼውም ጊዜ በላይ ለሀገራዊ ሰላም እጦት ምክንያት የሆኑ ችግሮቻችንን በትክክል ተረድተን ፤ በችግሮቹ ዙሪያ የጋራ ግንዛቤ ይዘን አለቅ ካለን የግጭት አዙሪት የሚያወጣንን መፍትሔ ለማፈላለግ አብዝተን የምንተጋበት ነው ።

ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ እውነታዎችን በአግባቡ ተረድተን እንደ ሀገር የጀመርነው ለውጥ በመላው ሕዝባችን ውስጥ የፈጠረውን መነቃቃት እንደ አንድ ታሪካዊ የመሻገሪያ አቅም ወስደን ከለውጡ ዋዜማ ጀምሮ እንደ ሀገር ያለምናቸውን የለውጥ ህልሞች እውን ለማድረግ በተሻለ የኃላፊነት መንፈስ የምንቀሳቀስበት ነው ።

ታሪካዊ ጠላቶቻችን እና በየዘመኑ ድህነትን አሸንፈን ለመውጣት የምናደርገው ጥረት ሰላም የሚነሳቸው ኃይሎች በእያንዳንዱ የለውጥ ክስተት ማግስት የውስጥ መሻታችንን ለማዳፈን ብዙ ርቀት ተጉዘዋል። በዚህም በብዙ ትውልዶች መስዋእትነት ዛሬ ላይ የደረሰችውን ሀገራችንን ሕልውና ተፈታትነዋል።

ያልተገራ ፍላጎት ካላቸው የሀገር ውስጥ ኃይሎች ጋር በመናበብና በመቀናጀት ጭምር ለብዙ ወንድሞቻችን ሞት እና የአካል ጉዳት ፣ መፈናቀል እና ስደት ፣ ከፍ ላለ የሀገር ሀብት ውድመት ምክንያት ሆነዋል። የለውጡን ግለት በማቀዛቀዝ በዜጎች ሀገራዊ ተስፋ ላይ ጥርጣሬ ጭረዋል።

ለጠላቶቻችን የጥፋት ሴራ አቅም በመሆን የሚያገለግለው እንደ ሀገር በየዘመኑ ብዙ ዋጋ ያስከፈለን የፖለቲካ ባህላችን፣ ዛሬም በ21ኛው ክፍለ ዘመን ብዙ ያልተገባ ዋጋ እንድንከፍል አስገድዶናል። እንደ ሀገር ችግሮችን ተነጋግሮ መፍታት የሚያስችሉ ባህላዊና መንፈሳዊ እሴቶች ቢኖሩንም፤ ለእነሱ ቅድሚያ ሰጥተን መንቀሳቀስ አለመቻላችን “ሸክላ ሠሪ በገል ይበላል” እንደሚባለው ሆኖብናል፡፡

በየዘመኑ የነበሩ ትውልዶች የቱን ያህል መስዋእትነት ከፍለው ባለሀገር እንዳደረጉን በየእለት ትርክታችን አብዝተን እየተረክን ፣ ከትርክት ባለፈ በልዩነቶቻችን ዙሪያ ቁጭ ብሎ መነጋገር ባለመቻላችን ፣ የትውልዶችን መስዋእትነት በሚፈታተን ፣ ሀገርን እንደ ሀገር የህልውና ስጋት ውስጥ በሚጨምር ያልተገባ መንገድ ላይ ቆመን እየዳከርን ነው።

ይህንን እንደጥላ የሚከተለንን እና ብዙ ዋጋ እያስከፈለን ያለውን ሀገራዊ የሰላም ችግራችንን ተሻግረን ለራሳችንም ሆነ ለመጪዎቹ ትውልዶች የተሻለች ሀገር ለመፍጠር አሁን በእጃችን ያለውን ሀገራዊ የምክክር መድረክ በአግባቡ ልንጠቀምበት ይገባል። በተለይም የተለያዩ ፍላጎት ያላቸው የፖለቲካ ቡድኖች ፍላጎታቸውን ዘለቄ ለሆነ ሀገራዊ ሰላም እና ለሕዝባችን የመልማት ፍላጎት መስዋእት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

መላው ሕዝባችንም የእሱም ሆነ ፤ በዘመናት መካከል ትውልዶች የተመኙት የበለጸገች ሀገርን የማየት ተስፋ እውን ሊሆን የሚችለው የተለያዩ ፍላጎቶችን ማጣጣም የሚያስችል አዲስ የፖለቲካ አስተሳሰብ እንደ ሀገር መፍጠር ስንችል መሆኑን በመረዳት ሕዝቡ ራሱን ለዚህ እውነታ ማዘጋጀት፤ አስተሳሰቡ ገዥ እንዲሆን ሁለንተናዊ ጫና መፍጠር ይጠበቅበታል ።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ዘላቂ ሰላም በማስፈን ወደ ልማት በሙሉ ጉልበት ለመግባት

**ሙዘይን ዘኢትዮጵያ**

የለውጡ መንግሥት በሕዝብ ድምፅና ይሁንታ ኢትዮጵያን ማስተዳደር ከጀመረ እነሆ አራት ዓመት ሊሞላው ነው። በነዚህ ዓመታትም በተቻለው አቅም የሕዝቡን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ በርካታ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል። በነዚህ አጭር ጊዜያት ውስጥ በተሠሩ ሥራዎች በርካታ ለውጦች ሊመጡ ችለዋል። እንዲያም ሆኖ ግን አሁንም ኅብረተሰቡ የሚያነሳቸው የተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ ተመልሰዋል ማለት አይቻልም።

በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ውስብስብና ውጥንቅጡ የበዛ የሕዝብ ጥያቄን መመለስ እንደማይቻል ልብ ማለት ይገባል። ምክንያቱም በየትኛውም ሀገር ውስጥ ቢሆን አዲስ የለውጥ መንግሥት ሲመጣ እነዚህን ሁሉ የተለያዩ የሕዝብ ጥያቄዎች በአንድ ጊዜ መመለስ ስለማይቻል እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ጊዜ፣ ሂደትና ከሕዝቡ በኩል ደግሞ ትእግስት ይጠይቃል፡፡ ይህ ሲባል ግን እንደው የለውጡ መንግሥት እድሜው አጭር ቢሆንም ሕዝቡ አይጠይቅ ማለት አይደለም።

የሕዝብ ጥያቄ ዲሞክራሲያዊም፤ ሰብአዊም መብት ነው። መንግሥትም ቢሆን የሕዝቡን ጥያቄዎች መቀበልና ለመመለስ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል። በተመሳሳይ ሕዝቡም ጥያቄዎቹን በሰለጠነና በሰላማዊ መንገድ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ያኔ መንግሥት መሠረታዊና አንገብጋቢ የሕዝብ ጥያቄዎችን ደረጃ በደረጃ ለመመለስ ጥረት ያደርጋል። ሕዝቡም ለጥያቄዎቹ በቂ መልስ እያገኘ ይመጣል።

ይህ ሆኖ ሳለ አንዳንድ የፖለቲካ ቡድኖችና ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች የኃይል አማራጭን ወስደውና ትጥቅ አንግበው ለጥያቄያቸው መልስ ለማግኘት የሚታትሩ በየአቅጣጫው ተፈጥረዋል። ዲሞክራሲያዊ መንገድን ትተው በምርጫ ወደስልጣን የመጣን መንግሥት በኃይል ለመጣል ላይ ታች የሚሉ ጥቂት አይደሉም። ከነዚህ ውስጥ በአማራ ክልል የሚንቀሳቀሰውና ራሱን ፋኖ ብሎ የሚጠራው እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል የሚንቀሳቀሰው የሸኔ ቡድን በዋናነት ይጠቀሳሉ።

እነዚህ ቡድኖች መንግሥት በተደጋጋሚ ያቀረበላቸውን የሰላም ጥሪ ወደጎን በመተውና የኃይል አማራጭን ወስደው መንቀሳቀስ ከጀመሩ ሰንበትበት ብለዋል። በዚህም መሸሸጊያቸው ባደረጉት ሕዝብ ላይ ይህ ነው የማይባል በደል ሲያደርሱና ሰላሙን ሲያደፈርሱ ቆይተዋል፤ አሁንም በዚህ ተግባራቸው ቀጥለዋል። በዚህም የኅብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት ከማናጋት ውጪ አንድም የፈየዱት ነገር የለም፡፡

በዚሁ ሥራቸው ምክንያት ነው እንግዲህ መንግሥት የኅብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅ ሲል የተለያዩ እርምጃዎችን ሲወስድ የቆየው፡፡ በመጀመሪያ መንግሥት እነዚህ ቡድኖች ወደ ሰላም አማራጭ እንዲመጡና ችግራቸውን በውይይት እንዲፈቱ በሩን ክፍት አድርጓል፡፡ ነገር ግን ሁለቱም ታጣቂ ቡድኖች የኅብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት ከማወክ፣ ከመግደልና ከማሰቃየት ወደኋላ አላሉም፡፡ ለዛም ነው መንግሥት እስካሁን ድረስ እነዚህ ቡድኖች ላይ ርምጃ እየወሰደ የሚገኘው፡፡

በዚህም በርካታ የቡድኑ አባላት በየጊዜው እየተደመሰሱና ገሚሶቹም እጃቸውን ለመንግሥት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ይህም በሁለቱም ክልሎች አንፃራዊ ሰላም እየሰፈነ እንዲመጣ አድርጓል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ለሕዝቡ ራስ ምታት የሆኑ ታጣቂ ቡድኖችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በመደምሰስ በክልሎቹ አስተማማኝ ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ ከመንግሥት በኩል ጠንካራና የተደራጁ ሥራዎችን መስራት ያስፈልጋል፡፡

ከነዚህ ውስጥ አንዱና አሁንም መንግሥት እያከናወነ ያለው ተግባር ሰላማዊ መንገድን መርጠውና ሲሠሩት በነበረው እኩይ ሥራ የተፀፀቱ የታጣቂ ቡድኖች አባላትን ወደ ተሃድሶ ማእከላት በማስገባትና በቂ ስልጠና በመስጠት ወደ ኅብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ ሥራም በርካታ የታጣቂ ቡድኖቹ አባላት እጃቸውን በሰላም ለመከላከያ ሠራዊት በመስጠት ወደ ተሃድሶ ማእከላት እየገቡ ነው፡፡ ይህንኑ ተግባር በማየት ሌሎችም ወደ ተሃድሶ ማእከላት እንደሚገቡ ይጠበቃል፡፡

መንግሥት ባደረገው የሰላም ጥሪ በርካታ የታጣቂ ቡድኖቹ አባላት ወደ ተሃድሶ ማእከላት እየገቡ ነው። ይህ ሊሆን የቻለው ታዲያ መንግሥት አሁንም ቢሆን ለሰላም በሩ ክፍት መሆኑን በተደጋጋሚ በመግለፁና በሰላምና ፀጥታ ጉዳይ ጠንካራ ሥራዎችን በመሥራቱ ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ የቡድኑ አባላትም ቢሆኑ ወደተሃድሶ ማእከላት በብዛት እየገቡ ያሉት ይህ የሰላም አማራጭ አዋጭ እንጂ አከሳሪ አለመሆኑን በመረዳት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ዛሬም፣ ነገም፣ ከነገ ወዲያም ይህን የሰላም አማራጭ እድል ተጠቅመው ወደ ተሃድሶ ማእከላት በርካታ የታጣቂ ቡድኖቹ አባላት እንደሚገቡ ይጠበቃል፡፡

አገናዝቦና በብስለት ወስኖ ወደ ተሃድሶ መግባት በብዙ መልኩ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም፡፡ ይህን ወስነው ወደ ተሃድሶ ማእከላት የሚቀላቀሉ የቡድኑ አባላት ተገቢውን ስልጠናና ትምህርት ወስደው ከጥፋታቸው ተምረው ዳግም ወደ ኅብረተሰቡ ተቀላቅለው የበደሉትን ሕዝብና መንግሥት ዳግም መካስ እድል ይፈጠርላቸዋል። ካላስፈላጊ የህይወት መስዋእትነትም ይድናሉ፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ልክ እንደማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል በመረጡት የሥራ ዘርፍ ተሰማርተው ጥረው ግረው የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ህይወት ለመቀየር ምቹ አጋጣሚ ይፈጠርላቸዋል፡፡ የልማቱ ተሳታፊ በመሆንም ጭምር የራሳቸውን አስተዋፅኦ የሚያበረክቱበት እድል ሰፊ ነው።

ስለዚህ የታጣቂ ቡድኖቹ አባላት በስፋት ወደ ተሃድሶ ማእከላት እንዲገቡና ለእነርሱም ሆነ ለኅብረተሰቡ ሰላማዊ ምህዳር እንዲፈጠር ከራሳቸው ከታጣቂ ቡድኑ አባላት፣ ከሕዝቡና ከመንግሥት ብዙ ሥራዎች ይጠበቃሉ። የታጣቂ ቡድኑ አባላት እያደረጉት ያለው የኃይል እንቅስቃሴ የህይወት ዋጋ እንደሚያስከፍልና በዚህ መንገድ ስልጣን መያዝ እንደማይቻል ልብ ሊሉ ይገባል፡፡ ጊዜው የውይይትና በሃሳብ የማሸነፍ ነውና ይህንኑ የሰላም አካሄድ በመከተል በሃሳብ የበላይነት በማመን በዚሁ መንገድ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፡፡ ያኔ ተገቢውን ስልጠናና ምክር አግኝተው ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማድረግ ይችላሉ።

በዲሞክራሲና በሰለጠነ መንገድ ጥያቄያቸውን ማቅረብና አላማም ካላቸው አላማቸውን ለማሳካት በዚሁ መንገድ መንቀሳቀስ ይችላሉ፡፡ በዚህ ሰላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ከሆነ ሕዝቡም ቢሆን ፖለቲካዊ አካሄዳቸውን፣ ዓላማቸውንና ሃሳባቸውን ለማዳመጥ ዝግጁ ይሆናል፡፡

ኅብረተሰቡም ቢሆን እነዚህ ታጣቂ ኃይሎች በሰላማዊ መንገድ እጃቸውን ሰጥተው ወደ ተሃድሶ ማእከላት እንዲገቡ በየትኛውም አጋጣሚ ቢሆን ከመንግሥት ጋር በትብብር መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ እነዚህ ታጣቂ ቡድኖች መሸሸጊያቸው በአብዛኛው ሕዝቡ ነውና አባላቱን መንጥሮ በማውጣቱ ሥራ ኅብረተሰቡ ቀና ትብብር ሊያደርግ ይገባል። አባላቱ ለመከላከያ ሠራዊቱ በሰላም እጃቸውን እንዲሰጡ መጠቆምም ይኖርበታል፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ የታጣቂ ቡድኖቹ አባላት ወደ ተሃድሶ ማእከል እንዲገቡና በሰላማዊ መንገድ እንዲታገሉ ምክር መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

መንግሥትም እስካሁን ድረስ እየሠራው ያለው ሥራ እንዳለ ሆኖ የታጣቂ ቡድኑ አባላት አሁንም ወደ ተሃድሶ ማእከላት በብዛት እንዲገቡ ተጨማሪ የቤት ሥራዎችን መሥራት ይኖርበታል፡፡ በተለይ ደግሞ ይህ አካሄድ አዋጭና አላስፈላጊ የህይወት መስዋእትነትን የሚቀንስ መሆኑን በመረዳት ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት አለበት፡፡ በተለይ ደግሞ አባላቱ ወደ ተሃድሶ ማእከላት እንዲገቡ በማድረጉ ሂደት ሕዝቡ ቁልፍ ሚና ስለሚጫወት ከሕዝቡ ጋር እጅና ጓንት ሆኖ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡

በሌላ በኩል የታጣቂ ቡድኖቹ አባላት ወደ ተሃድሶ ማእካላት ከገቡ በኋላ ተገቢውን ስልጠናና ትምህርት አግኝተው ወደ ኅብረተሰቡ ከተቀላቀሉ በኋላ ፍፁም ሰላማዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉና ተመልሰው ወደ በፊቱ እንቅስቃሴያቸው እንዳይገቡ የማያቋርጥና ተከታታይነት ያለው ሥራ ከኅብረተሰቡ ጋር በመሆን ማከናወን አለበት፡፡ ለዚህ ስራ ታዲያ በሁለቱም ክልሎች እስከታችኛው መዋቅር ድረስ ያሉ አመራሮች የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

የተሃድሶ ሥራውን በቅንጅትና በትብብር መሥራት የሚቻል ከሆነ አላስፈላጊ የህይወት መስዋእትነትን በመቀነስ ወደ ሰላማዊ እንቅስቃሴ መመለስ ይቻላል፡፡ ይህ ሰላማዊ ሁኔታ ደግሞ የሚፈለገውን ልማት ለማፋጠን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ያኔ በሁለቱም ክልሎች ያሉ ሕዝቦች የሰላም አየር ተንፍሰው በልማታዊ እንቅስቃሴዎች ንቁ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡

የታጣቂ ቡድኖቹ አባላት መንግሥት ያቀረበላችሁን የሰላም አማራጭ መንገድ በመከተል ወደዚሁ መስመር እንደሚቀላቀሉ ተስፋ ይደረጋል፡፡ ወደተሃድሶ እየተቀላቀሉ ያሉትም ተገቢውን ስልጠናና ትምህርት ወስደው ሀገራቸውን ለመካስ ራሳቸውን ዝግጁ ማድረግ አለባቸው፡፡

# ነፃ ሃሳብ

# ለሰው ልጆች ደህንነት የሰው ሰራሽ አስተውህሎ ልጓም ማበጀት!!

**አዲስ መኮንን**

ዓለም በማይገመት የቴክኖሎጂ ለውጥ አብዮት ውስጥ ይገኛል። የሰው ሠራሽ አስተውህሎ፣ የሮቦቲክስ ቴክኖሎጂ እና የበይነ-መረብ ቁሶች አዲስ የቴክኖሎጂ አብዮት እየፈጠሩ ነው። በተለይ የሰው ሠራሽ አስተውህሎ ብዙዎች ስለ ወደፊት እጣ ፈንታቸውና ሰብዓዊነት እንዲያስቡ ሳያደርጋቸው አልቀረም።

የሰው ሠራሽ አስተውህሎ እያደገ እና ጥቅም ላይ እየዋለ ያለበት ፍጥነት ልጓም ስለማበጀት እንድናስብ ያስገድደናል። ቴክኖሎጂው ወደፊት የሰዎችን ሥራ በመቀማት ሥራ አጥ ሊያደርጋቸው "ይችላል" ወይስ "አይችልም" እንዲሁም ደግሞ ሰዎችን በቁጥጥሩ ስር በማድረግ ሰብዓዊነት ላይ አደጋ ሊደቅን "ይችላል" ወይስ "አይችልም" የሚለው ጉዳይ የብዙዎች ስጋት እየሆነ መጥቷል። ፒው የተሰኘ የምርምር ተቋም በአሜሪካ ሀገር ባጠናው ጥናት በሀገሪቱ ከ52 ከመቶ በላይ ሰዎች ቴክኖሎጂው ሰዎችን በመቆጣጠር አደጋ ይደቅናል የሚል ስጋት እንዳላቸው ተናግረዋል።

ርግጥ ነው ቴክኖሎጂው በአስደንጋጭ ሁኔታ የሰዎችን አዕምሮ ቀድቶና ተምሮ ሰዎችን ሊበልጥ እየተገዳደረ ነው። አንዳንድ ባለሙያዎች በቅርብ ዓመታት ውስጥ የሰው ሠራሽ አስተውህሎ የሰዎችን የማሰብ ችሎታ ይበልጣል የሚል ግምት ያስቀምጣሉ። ዛሬ የሰው ሠራሽ አስተውህሎ የተገጠመለት ሮቦት ቀዶ ጥገና እየሰራ ነው፡፡ መኪናዎች በሰው ሠራሽ አስተውህሎ በታገዘ ቴክኖሎጂ ሹፌር ሳያስፈልግ ሰዎችን ከቦታ ወደ ቦታ ማንቀሳቀስ ጀምረዋል።

የሰው ሠራሽ አስተውህሎ የቋንቋ ሞዴል ጥናታዊ ጽሑፎችን ጥንቅቅ አድርጎ እስከ ማዘጋጀት ደርሷል። በሰው ሠራሽ አስተውህሎ የሚሳሉ ስዕሎች አጃኢብ የሚያሰኙ ናቸው። "ሶራ" የተሰኘው የሰው ሠራሽ አስተውህሎ፣ ሃሳብ ብቻ ሰጥተነው ጥንቅቅ ያለ ፊልም ሰርቶ ያስረክበናል። የሰዎችን ሥራ ሁሉ መሥራት የተማረ ማሽን ከሰው አስበልጦ ነገሮችን መከወን ደረጃ ላይ ደርሷል።

ሰሞኑን ደግሞ ቻት ጂ ፒ ቲ 4 ኦ (ChatGPT 4O) ደረጃውን ከፍ አድርጎ በጽሁፍ፣ በድምፅ እና በምስል ከሰዎች ጋር መግባባት ጀምሯል። አንድ ሰው ያለበትን ቦታ፣ የለበሰውን ልብስ፣ በአካባቢው ያሉ ቁሶችን ጥንቅቅ አድርጎ በመመልከት ማብራራት የቻለበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ከጎናችን እንዳለ አንድ ሰው ሆኖ በትክክል ማዋራት ጀምሯል። ለዚህ ነው ቴክኖሎጂው በብዙዎች ዘንድ ስጋትን የፈጠረው እና ስለ ሕግ እንዲያስቡ እያስገደደ ያለው።

ርግጥ ነው ቴክኖሎጂው ተመሳሳይ እና በሰዎች ዘንድ አሰልቺ የሆኑ ሥራዎችን በማቀላጠፍ ዓይነተኛ ሚና እየተጫወተ ነው። የሰዎችን ሕይወት በእጅጉ እያቀለለ ነው። በጣም ባጠረ ጊዜ እና ወጪ በሚቆጥብ ሁኔታ ለሰው ልጅ ግልጋሎት እየሰጠ ነው። ለሰው ልጅ አደጋ የሆኑ ሥራዎችን ተክቶ በመሥራት ሰዎችን ከአደጋ መጠበቅ አስችሏል።

በቴክኖሎጂው ዙሪያ የሚነሳው ሌላኛው ስጋት የሰው ሠራሽ አስተውህሎ መድሎ ነው። ሶፍትዌር የሰጡትን ይቀበላል። ሰው ያዘዘውን ይፈፅማል። በተሰጠው መረጃ ልክ ሥራዎችን ይከውናል። ነገር ግን ሰው መረጃ ሲሰጠው በሰውየው ፍላጎት መሠረት አድልዎ እንዲሰራ አድርጎ መረጃ ሊመግበው ይችላል። አድልዎው በፆታ፣ በእድሜ፣ በቆዳ ቀለም እና በሌሎችም ምክንያቶች እንዲሰራ ተደርጎ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ባደጉት ሀገራት የቆዳ ቀለም ልዩነት በተለያዩ አካባቢዎች ዛሬም አጀንዳ ሆኖ ቀጥሏል። አንድ መሥሪያ ቤት የሥራ ማስታወቂያ ቢያወጣ እና የቅጥር ሂደቱ ሲስተም እንዲፈፅመው ቢደረግ የፈተናውን ሂደት ለተፈለገው አካል እንዲያዳላ አድርጎ ማዘዝ ይቻላል። ለሴት ወይም ለወንድ፣ ለቀይ ወይም ለጥቁር፣ እድሜያቸው ወጣት ለሆኑ ወይንም ትንሽ ገፋ ላሉ ተደርጎ ወዘተ ሊዘጋጅ ይችላል። ይህ የሰው ሠራሽ አስተውህሎ አድሎ የብዙዎች ስጋት ነው። ይህም አንዱ አሳሳቢ ጉዳይ ሆኗል።

**ይህ እንቅስቃሴ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም ያላትን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ሲሆን ባለቤት ተሰጥቶት ቴክኖሎጂውን ለማሳደግ፣ ለመጠቀምና ለመቆጣጠር የሚያስችል እድል ይፈጥራል**

የሰው ሠራሽ አስተውህሎ የሰዎችን ግላዊ ደህንነት በመጋፋት ረገድም ስሙ ጎልቶ ይነሳል። በፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ለሰው የተለያዩ የሕግ ከለላዎች ይሰጡታል። ከቦታ ቦታ ያለገደብ የመንቀሳቀስ መብት አንዱ ነው። ነገር ግን አሁን እየመጡ ያሉ የደህንነት ካሜራዎች የሰዎችን ነፃነት እስከ መጋፋት ደርሰዋል። ይህ ጉዳይ ሕግ ሊበጅለት ይገባል። የት የት አካባቢ እንዲህ ያሉ ሥርዓቶች መዘርጋት እንዳለባቸው፣ የትኞቹ ቦታዎች ላይ ደግሞ መገጠም እንደሌለባቸው በሕግ ሊደነገግ ይገባል።

የአውሮፓ ህብረትም ባፀደቀው የሰው ሠራሽ አስተውህሎ ሕግ ላይ በጣም ከፍተኛ ጥበቃ ከሚያስፈልጋቸው ቦታዎች ውጭ የሰዎችን የፊት ገፅታ መመዝገብን ከልክሏል። ይህ ከሰዎች ደህንነት ጋር የተያያዘ ነው። እኛ ሀገር ግን አሳንሰር ወይም ሊፍት ላይ ሳይቀር ካሜራዎችን የመግጠም ልምድ እየታየ ነው። እነዚህ ችግሮች የሚቀረፉት በሕግ ነው።

ቴክኖሎጂ በማያቋርጥ የለውጥ ጉዞ ውስጥ የሚያልፍ እና እድሜውም በጣም አጭር ነው። ይህ ማለት ዛሬ የተፈጠረ አዲስ ቴክኖሎጂ በቀጣዩ ዓመት አዳዲስ ነገሮች ተጨምረውበት አድጎ እና ተለውጦ ሌላ ታሪክ ውስጥ ገብቶ ነው የሚገኘው። በዚህ ተለዋዋጭ የቴክኖሎጂ ዓለም ውስጥ ሀገራት የዜጎቻቸውን መብት ለማስጠበቅ ሲባል ቢችሉ የቴክኖሎጂውን የእድገት ደረጃ አስቀድመው በመተንበይ ካልሆነም ደግሞ ከቴክኖሎጂው እኩል በመራመድ "ሕግ" የተሰኘ ልጓም ሊያበጁለት ግድ ይላቸዋል።

አንዳንድ የዘርፉ ባለሙያዎች የቴክኖሎጂን እድገት ሊገድብ ስለሚችል ቴክኖሎጂ የሚመራበት ሕግ ቀድሞ መውጣት የለበትም ብለው ይከራከራሉ። ተገቢው አካሄድ ቴክኖሎጂውን እየተከተሉ የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት እንደሆነ ያምናሉ። ሕግ ቅድሚያ ከተዘጋጀ ቴክኖሎጂው የሚያመጣቸውን አዳዲስ ግኝቶች እየገደበ ተጠቃሚነትን ያስቀራል ብለው ይከራከራሉ። እንዲህ ያሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ቦታ ተከልሎላቸው እዚያ ውስጥ እየዳበሩ መሄድ አለባቸው ብለው የሚከራከሩም አሉ። ያም ሆነ ይህ ግን የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት ላይ ሁሉም ይስማማሉ።

የሰው ሠራሽ አስተውህሎ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ተደጋጋሚና አሰልቺ ሥራዎችን ከመተካት ጀምሮ በጣም ጥንቃቄ በሚጠይቀው የሕክምና ዓለም ውስጥ ሳይቀር ግልጋሎት እየሰጠ ይገኛል። ቴክኖሎጂው በመከላከያ፣ በትምህርት፣ በፍትህ ሥርዓት፣ በመዝናኛ፣ ወዘተ በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል።

ሀገራት የቴክኖሎጂውን አዝማሚያ እና እየተጓዘበት ያለውን ፍጥነት በማየት የተለያዩ ርምጃዎችን እየወሰዱ ይገኛሉ። የአውሮፓ ህብረት ፓርላማ የሰው ሠራሽ አስተውህሎ ረቂቅ ሕግ ለፓርላማው አቅርቦ አፅድቋል። ሕጉ የሰው ሠራሽ አስተውህሎ ቴክኖሎጂን የማይፈቀዱ፣ ከፍተኛ አደጋ ያላቸው እና ዝቅተኛ አደጋ ያላቸው በሚል በሶስት ምድቦች አስቀምጧል። የማይፈቀዱ ያላቸው በማህበረሰቡ ውስጥ እንደ ስጋት የሚቆጠሩትን ነው። ሕፃናት አደገኛ ባህሪ እንዲላበሱ የሚያደርጉትን በዚህ ምድብ ውስጥ አካትቶታል።

ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ የሚባሉት ደግሞ ወደ ገበያ ከመውጣታቸው በፊት የአውሮፓ ህብረት ከፍተኛ ባለስልጣናትን ፍቃድ የሚጠይቅ ተብሎ ተለይቷል። የቅጥር ምልመላ፣ የሕግ ማስከበር፣ የድንበር ጥበቃ እና በመሳሰሉት ላይ የሚተገበሩ የሰው ሠራሽ አስተውህሎ ውጤቶች በዚህ ምድብ ውስጥ የተካተቱ ናቸው። ሕጉ ቀጣዮቹን ሂደቶች ሲያልፍ ወደ ሥራ ይገባል ተብሎ ይጠበቃል።

ብራዚል በረቂቅ ደረጃ ባዘጋጀችው የሰው ሠራሽ አስተውህሎ ሕግ ተጠቃሚዎች ከሰው ሠራሽ አስተውህሎ ጋር እየተመላለሱ መሆናቸውን፣ ውሳኔ እንዴት እንዴት እንደሚሰጥና ምክረ ሃሳቦችን በምን መልኩ እንደሚያቀርብ የማወቅ መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። የሰው ሠራሽ አስተውህሎ ውሳኔዎች በሰው ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ከሆኑ (ለምሳሌ ራሳቸውን የሚነዱ መኪኖች፣ ቅጥር፣ የሂሳብ ጉዳዮች) የሰዎችን ጣልቃ ገብነት መጠየቅ የሚያስችል መብት ይሰጣቸዋል። ቴክኖሎጂውን የሚያለሙ አካላት ደግሞ የጉዳት ትንተና እንዲሰሩና እንዲከታተሉ ያስገድዳል። በሰዎች ላይ ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ጉዳዮችን ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

ቻይና የሰው ሠራሽ አስተውህሎ ረቂቅ ሕግ አሳትማ ለሕዝብ አስተያየት ክፍት አድርጋለች። ቴክኖሎጂው እውነተኛ እና ትክክለኛ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ ላይ ያተኮረ ሲሆን የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም እሴቶችን ማንፀባረቅ አለበትም ይላል። የሰው ሠራሽ አስተውህሎው ለሰራቸው ሥራዎች ውጤት (output) አበልፃጊው ሙሉ ኃላፊነት እንደሚወስድም ይደነግጋል። ከአዕምሯዊ ንብረት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችም ትኩረት ተሰጥቷቸዋል።

ጣልያን፣ ጃፓን፣ እስራኤል እና የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች በሀገራቸው ሁኔታ ልክ የሰው ሠራሽ አስተውህሎ ሕግ እያረቀቁ ይገኛሉ። ጣልያን በዲጂታላይዜሽን ምክንያት ሥራቸውን ያጡ ዜጎችን ለመደጎም የሚያስችል አሠራር እየዘረጋችም ትገኛለች። ሁሉም ሀገራት ግን የዳታ ጥበቃ (Data) ላይ ትኩረታቸውን ያደረጋሉ።

ኢትዮጵያም የቴክኖሎጂውን ጠቃሚነት ታሳቢ በማድረግ የሰው ሠራሽ አስተውህሎ ኢንስቲትዩት አቋቁማ ቴክኖሎጂውን ተግባራዊ እያደረገች ትገኛለች። በኢትዮጵያ የተለያዩ ዘርፎች ከፍተኛ የማዘመን ሥራ ይጠይቃቸዋል። የጤናው ዘርፍ፣ ትምህርት፣ ግብርና፣ መከላከያ፣ ትራንስፖርት፣ ፋይናንስ እና ሌሎችም ዘርፎች ይህንን ቴክኖሎጂ ይፈልጋሉ።

በርካታ ሥራዎች በሰው ሠራሽ አስተውህሎ የተደገፈ የኦቶሜሽን ሥራ ካልተሰራላቸው ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት፣ ምርትን ማሳደግ እና በጥቅሉ ሁለንተናዊ እድገት ማስመዝገብ አዳጋች ይሆናል። ይህ ብቻ ሳይሆን ሉላዊው ዓለም እየተራመደበት ካለው የቴክኖሎጂ መንገድ መነጠል አዳጋች በመሆኑ በተቻለ ፍጥነት በራስ አቅም ከቴክኖሎጂ እኩል መጓዝ የግድ ይላል። ለዚህም ይመስላል ኢትዮጵያ ከሌሎች ተቋማት ጋር በተደራቢነት መሥራት እየተቻለ ልዩ ትኩረት በመስጠት የሰው ሠራሽ አስተውህሎ ተቋም ያቋቋመችው።

ይህ እንቅስቃሴ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም ያላትን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ሲሆን፣ ባለቤት ተሰጥቶት ቴክኖሎጂውን ለማሳደግ፣ ለመጠቀምና ለመቆጣጠር የሚያስችል እድል ይፈጥራል። ሀገራት በዚህ ዘርፍ ለዜጎች የግል ዳታ ጥበቃ ልዩ ትኩረት የሚሰጡ ሲሆን ኢትዮጵያም የግል ዳታ ጥበቃ አዋጅን በማርቀቅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲፀድቅ አድርጋለች።

ይህ በዘርፉ የተደረገ ትልቅ ርምጃ ሲሆን ዜጎች በኤሌክትሮኒክ የተመዘገቡ መረጃዎቻቸው ወደ ሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፉ ጥበቃ እንደሚደረግላቸውና እምነት እንዲኖራቸው ያስችላል። በዲጂታል ዓለም ውስጥ የዲጂታል እምነት መፍጠር ትልቁ ሥራ ነው።

ቴክኖሎጂውን ከመጠቀም ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ውስጥ ትልቅ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ክህሎት ክፍተት ይስተዋላል። በአንድ በኩል በዘርፉ በዓለም አቀፍ መድረክ ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ኃይል ያለ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ቴክኖሎጂው ከነመፈጠሩም ያለማወቅ ክፍተቶች ይስተዋላሉ።

ይህንን ክፍተት ለመሙላት በትምህርት ካሪኩለም ውስጥ ከማካተት ጀምሮ የተለያዩ ርምጃዎችን በመውሰድ የክህሎት ክፍተቱን መሙላት አስፈላጊ ሲሆን የሕግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀትም ለነገ የማይባል የቤት ሥራ ነው። ሕግ ሲዘጋጅም ማህበረሰቡ ያለበትን ደረጃ ከግምት ውስጥ ያስገባ እና ይህንን የዲጂታል ክህሎት ክፍተት ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል።

የኢትዮጵያ የሰው ሠራሽ አስተውህሎ ተቋም (የኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንስቲትዩት) የሰው ሠራሽ አስተህውሎ ፖሊሲ ለማዘጋጀት እንቅስቃሴ ላይ ነው። ፖሊሲው እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንደሚዘጋጅ ተስፋ እናደርጋለን።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## «ወጣት የነብር ጣት» የሚለውን ቢሂል ያስመሰከሩ የቡታጅራ ወጣቶች

ማህሌት አብዱል

መንግሥት ወጣቶች ሥራ ፈጣሪ በመሆን ራሳቸውንም ሆነ ሀገራቸውን ከድህነት እንዲያወጡ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ላይ ይገኛል። በተለይም ደግሞ ትምህርታቸውን አጠናቀው ያለ ሥራ የተቀመጡ ወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ባላቸው ዘርፎች ላይ ተሰማርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከስልጠና ጀምሮ የፋይናንስ አቅርቦት፣ የማምረቻና መሸጫ ቦታ እንዲሁም የገበያ ትስስር በመፍጠር ረገድ በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ነው፡፡

ወጣቶች ተደራጅተው እየሰሩ ካሉባቸው የሥራ መስኮች መካከልም የከተማ ግብርና ሥራ ዋነኛው ነው፡፡ ክልሎች በተለይም በከተሞች አካባቢ ትምህርታቸውን አጠናቀው ያለ ሥራ የተቀመጡ ወጣቶች ወተት፣ በንብ ማነብና በዶሮ እርባታ ላይ በማሰማራት ረገድ ውጤታማ ሥራ እያከናወኑ ነው ያሉት፡፡

ከእነዚህም ክልሎች መካከል ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ተጠቃሽ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፕሬስ የጋዜጠኞች ቡድንም በቅርቡ በክልሉ እየተሰሩ ያሉ የግብርና ልማት ሥራዎች የመስክ ምልከታ ማድረጉ የሚታወስ ነው፡፡ ከእነዚህም የክልሉ አካባቢዎች መካከል የቡታጅራ ከተማ አንዱ ሲሆን በከተማዋ ወጣቶች ተደራጅተው በተለያዩ የግብርና ልማት ሥራዎች ላይ እያደረጉት ያለው የሥራ እንቅስቃሴ ምልከታ አድርጎ እንደሚከተለው ይዞ ቀርቧል፡፡

ወጣት አቤል ሙሉጌታ ቀሸት የንብ ማህበር መስራችና ሊቀ መንበር ነው፡፡ ተማሪ በነበረበት ወቅት አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፈው ከግብርና ባለሙያዎች ጋር ስለነበር ለግብርና ሥራ የተለየ ፍላጎት እንደነበረው ያስታውሳል፡፡ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀም የሚቀርባቸው የግብርና ባለሙያዎች እሱና ጓደኞቹ በንብ ማነብ ሥራ ቢሰማሩ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይነግሯቸዋል፡፡ ወጣት አቤል አዋጭነቱን ካጠና በኋላ ምክረ-ሃሳቡን ተቀበለና አራት ጓደኞቹን በማሰባሰብ ማህበር መሰረተ፡፡ እናም በቡታጅራ ከተማ አስተዳደር ግብርና ጽሕፈት ቤት እገዛ በከተማ በሚገኘው ሆስፒታል ባዶ ስፍራ ላይ አስር ባህላዊና ዘመናዊ ቀፎችን በማዘጋጀት የንብ ማነብ ሥራ መጀመራቸውን ይገልፃል፡፡

ወጣት አቤል እንዳሰበውም ሥራው ውጤታማ እየሆነና የሚያመርቱት ምርት በከተማው ነዋሪ ተወዳጅ እየሆነ ሲመጣ 200 ዘመናዊና ከ150 በላይ ባሕላዊ ቀፎ ማድረስ ቻሉ፡፡ ማር የማምረት አቅማቸው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ብቻ ከ1ሺ 500 ኪሎ ግራም በላይ ደርሷል፡፡


የከተማ አስተዳደሩ ከግብርና ቢሮ ጋር በመቀናጀት ለማህበሩ የገበያ ትስስር የተፈጠረላቸው መሆኑን የሚጠቅሰው ወጣት አቤል በአሁኑ ወቅት አንድ ኪሎ ወለላ ማር እስከ 600 ብር ድረስ ፤ እንጀራ ማር ደግሞ 500 ብር የሚሸጡ መሆናቸውን ያስረዳል፡፡ ማህበሩ በንብ ማነብ ሥራ ብቻ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ 13 ለሚሆኑ የከተማዋ ወጣቶች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል መፍጠር መቻሉንም ያመለክታል፡፡

ወጣት አቤል እንደሚለው፣ በአሁኑ ወቅት ማህበሩ የንብ ማነብ ሥራውን እየሰራ ያለው በተለመደውና በባሕላዊ መንገድ ነው፡፡ ይሁንና በቀጣይ ዓመት ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ አሰራራቸውን የማዘመን እቅድ ይዘው እየሰሩ ነው፡፡ ከከተማ ግብርና ጽሕፈት ቤት ጋር በመተባበር እስከ አንድ ሺ ዘመናዊ ቀፎ ለማድረስ አልመዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር ቡታጅራን የምስራቅ አፍሪካ የንብ ማዕከል ለማድረግ እየሰሩ ነው፡፡


ለዚህ ግባቸው መሳካት ግን የቦታ እጥረት ተግዳሮት ይሆንብናል የሚል ስጋት እንዳለባቸው ወጣት አቤል ተናግሮ ፤ ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ለከተማ አስተዳደሩ ጥያቄ ማቅረባቸውንና በቅርቡ ምላሽ ያገኛል የሚል ተስፋ እንዳለውም ያመለክታል። ‹‹አስፍተን ለመሥራት የፋይናንስ አቅም የሚጠይቅ በመሆኑ ፕሮፖዛል ነድፈን ብድር ለመጠየቅ አቅደናል›› ሲልም ያክላል፡፡



ወጣት አቤል ሙሉጌታ፣



ፋሲል አሕመድ (ዶ/ር)፣



በቡታጅራ ከተማ በንብ ማነብ ሥራ ላይ የተሰማሩ ማህበራት መኖራቸውን የሚናገረው ወጣት አቤል የእነሱ ማህበር ለሌሎቹ ማህበራት ስልጠና በመስጠትና ተሞክሮ በማካፈል እገዛ እያደረገ መሆኑንም ያስረዳል፡፡ ‹‹ህብረ ንብም በመስጠት የምናግዛቸውም አሉ›› በማለት ተናግሮ ወደፊት ዘመናዊ ማር የማቀነባበሪያ ማሽን የመትከል አላማ ስላላቸው ከእነዚህ ማህበራት ማር በመረከብ እና እሴት በመጨመር ወደ ውጭ የመላክ እቅድ እንዳላቸው ነው ያብራራው፡፡

ሥራውን ሲጀመር 12ኛ ክፍል ገና እንዳጠናቀቀ እንደነበር የሚያስታውሰው ወጣት አቤል በአሁኑ ወቅት በቢዝነስ ማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪውን እያጠና መሆኑን ይገልጻል፡፡ ይህም አሁን ለጀመረው የንብ ማነብ ሥራ ከፍተኛ ድጋፍ ያበረክትልኛል የሚል እምነት እንዳለው ይጠቅሳል፡፡ በተመሳሳይ ሌሎቹም የማህበሩ አባላት ለማህበሩ በሚጠቅሙ ዘርፎች ላይ ስልጠና እየወሰዱ መሆኑን አመልክቶ፣ ይህም ግላዊ የሆነ ክህሎትና አቅማቸውን ከማሳደግ ባሻገር ከተማዋን በንብ ማነብ በምስራቅ አፍሪካ ተመራጭ ለማድረግ ለወጠኑት እቅድ ወሳኝ ሚና እንዳለው ያስረዳል፡፡

ፋሲል አሕመድ /ዶክተር/ የቡታጅራ ከተማ ግብርና ጽሕፈት ቤት የግብርና ባለሙያ ነው፡፡ እሱ እንደሚለው፣ ጽሕፈት ቤቱ ወጣቶችን የሥራ ፈጣሪ ከማድረግ አኳያ በንብ ማነብ ብቻ ሳይሆን፣ በእንስሳት እርባታ፣ በዶሮ እርባታ መንደሮች ተመስርተው ብዙዎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዋነኝነት በንብ ማነብ ሥራ ከተማዋ የልሕቀት ማዕከል የሚያደርጋት አበረታች ውጤት እየተመዘገበ ነው፡፡ በከተማ ደረጃ ወደ 12 የንብ መንደሮች ያሉ ሲሆን፣ ቀሸት የንብ ማነብ ማህበር ደግሞ በከተማውም ሆነ በክልል ደረጃ በንብ ማነብ ሥራ ሞዴል ሆኖ የተመረጠ ነው፡፡

‹‹ማህበሩ በአሁኑ ወቅት ገና የጀመረ ቢሆንም በዓመት እስከ አንድ ሺ ኪሎ ግራም ማር የማምረት አቅም ላይ የደረሰ ሲሆን በቀጣይ ግን ከሶስትና አራት ሺ ኪሎ ግራም በላይ ይደርሳል ተብሎ ይጠበቃል›› የሚለው ዶክተር ፋሲል፣ ማህበሩ በሚሰራው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ከመንደሮቹ አልፎ የከተማው ነዋሪም በጊቢው ላይ አንድና ሁለት ቀፎ በመስቀል በንብ ማነብ ሥራ ላይ እየገባ መሆኑንም ያስረዳል፡፡

በተመሳሳይም ቡታጅራ በወተት ልማት ስሟ ገኖ እየወጣ መሆኑን የሚያነሳው ባለሙያው በአቅራቢያ ካሉ ዞኖች ባሻገር ከሌሎች አጎራባች ክልሎች ለሚመጡ አካላት ሞዴል በመሆንና ተሞክሮ በማካፈል ረገድ የላቀ ሥራ መሰራቱን ይጠቁማል፡፡ ‹‹32 ማህበራት በአንድ አካባቢ ላይ ተደራጅተው በከፍተኛ መጠን ወተት እየተመረተ ነው፣ በእነዚህ ማህበራት ደግሞ የሚሰሩት አብዛኞቹ የከተማዋ ወጣቶች ናቸው›› ሲል ያመለክታል፡፡ ከተማ አስተዳደሩ በከተማ ግብርና ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ ወጣቶች የሙያ፣ የቴክሎጂ፣ የሕክምና እና የስልጠና ድጋፍ እየሰጠ መሆኑን አስታውሰው፣ የብድር አቅርቦት እንዲያገኙም ከባንክ ጋር የማስተሳሰር ሥራም ጭምር በኃላፊነት እያከናወነ መሆኑን ነው የሚያብራራው፡፡

እነወጣት አቤል ከቦታ አቅርቦት ጋር የሚያነሱትን ጥያቄ በሚመለከት ዶክተር ፋሲል ተጠይቆ ‹‹የከተማ አስተዳደሩ ማህበሩን ከማደራጀት ጀምሮ አሁን እያመረተ ያለበትን ቦታ በመስጠት ድጋፍ አድርጓል፣ በተለየ መልኩ ለዓመታት ባዶ ቦታ አጥረው ያለ ሥራ ያስቀመጡ የመንግሥት ተቋማት መሬት ለተደራጁ ወጣቶች ሥራ እድል ፈጠራ እንዲውል ተደርጓል›› ሲል ያስረዳል፡፡ አክሎም ‹‹ማህበሩ በቀጣይ ለአቀደው የማስፋፊያ ፕሮጀክት መሳካት የከተማ አስተዳደሩ የተለመደ ትብብሩን ያደርጋል›› ብሏል፡፡ ይሁንና ከተማ እንደመሆኑ የመሬት አቅርቦት ውስን በመሆኑ ሰፊ ጥናት የሚፈልግ መሆኑን ከግንዛቤ ማስገባት ተገቢ ነው ባይ ነው፡፡

ከብድር አቅርቦት ጋር በተያያዘም ‹‹አበዳሪ ተቋማት ለተደራጁ ወጣቶች አፋጣኝ የብድር አገልግሎት እንዲሰጧቸው ከማድረግ በዘለለ በተለይ በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የበኩላችንን ድጋፍ እያደረግን ነው›› በማለት ይናገራል፡፡ በሌላ በኩል ማህበራቱ የገበያ ትስስር እንዲያገኙ ከማድረግ ባሻገር የተመረቱ ምርቶች እሴት ተጨምሮባቸው ወደ ተለያዩ ሀገራት ለመላክና ለሀገሪቱ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ የከተማ አስተዳደሩም ሆነ የክልሉ መንግሥት ትኩረት አድርጎ እየሰራ መሆኑን ዶክተር ፋሲል ያብራራል፡፡

በዚህ ረገድ በከተማዋ በአግሮ ፕሮሰሲንግ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች መኖራቸውን ጠቅሶ፣ ‹‹በተለይም ሶሲ የተሰኘው አግሮ ኢንዱስትሪ ከማህበራቱ ወተት ተረክቦ የማቀነባበር ሥራ በስፋት እየሠራ ነው፣ ይህም ወጣቶቹ የሚያመርቱት ምርት እንዳይባክን ከማድረግ ባለፈ ለሌሎች በርካታ የከተማዋ ወጣቶች ሥራ እድል በመፍጠር ረገድ አወንታዊ አስተዋፅኦ እያበረከተ ነው›› ሲልም ይገልፃል፡፡

በተመሳሳይ በንብ ማነብ ሥራ ተሰማርተው ማር ለማቀነባበር እቅድ ላላቸው እንደ እነአቤል ያሉ ወጣቶችን የብድርና የቴክኖሎጂ ድጋፍ በማድረግ የከተማ አስተዳደሩ እገዛ እንደሚያደርግ ያመለክታል። ‹‹በተለይ ቀሸት የንብ ማነብ ማህበር አሁን ካለው አያያዝ በመነሳት ከተማችንን በስፋት ያስተዋውቅልናል ብለን እናስባለን፣ እንዳውም የቡታጅራ ብራንድ ማር በማምረት የጎላ ሚና ይኖረዋል የሚል እምነት አለን›› ይላል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ማህበሩ ማር በማቀነባበር ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስችለውን አቅም በማጎልበት ረገድ ከማህበሩ አባላት ጋር ምክክር እያደረገ ስለመሆኑም ዶክተር ፋሲል የጠቆመው፡፡

እንደ ግብርና ባለሙያው ማብራሪያ፣ በከተማዋ መኖ አቀነባብሮ በከተማዋ ላሉ ማህበራት የሚያሰራጭ ወልታ የተሰኘ ዩኒየን አለ፡፡ ይሁንና ካለው ሰፊ ፍላጎት አንፃር አቅርቦቱ ዝቅተኛ በመሆኑ በአምራቾች ቅሬታ በተደጋጋሚ እየቀረበበት በመሆኑ የከተማ አስተዳደሩ በርከት ያሉ የመኖ ማቀነባበሪያዎችን እንዲቋቋሙ የበኩሉን ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ለመኖ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪው የሚውሉ የግብርና ውጤቶችንም በከተማ ዙሪያ ባሉ ወረዳዎች በስፋት የማምረት ሥራ እየተሰራ ነው፡፡ በተለይም ‹‹አልፋ አልፋ›› የተሰኘው መኖ እንዲሁም ለንብ ማነብ ጠቃሚ የሆኑና ማዓዛማ የሆኑ አባባና ሌሎች እፅዋቶችን ሁሉም በየጊቢው ላይ እንዲያመርት እየተደረገ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በዋናነት ለወጣቶች ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ድጋፍ እየተደረገ ነው ያለው፡፡

በንብ ማነብ ላይ የተሰማሩ ማህበራት አቅማቸውን በማሳደግ ሰም የማተም፣ ንግስት ንብ እያባዙ ለሌሎች አዳዲስ ሥራ ፈጣሪ ወጣቶች የማሰራጨት ሥራ እያከናወኑ መሆኑን ዶክተር ፋሲል ያነሳል። በተጨማሪ ማር መጭመቂያ ማሽን እንዲያገኙ የከተማ አስተዳደሩ የበኩሉን ጥረት እያደረገ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጋዜጠኞች ቡድን በከተማዋ ያሉ ወጣቶች በግብርናም ሆነ በሌሎች የሥራ መስኮች ተሰማርተው ራሳቸውንም ሆነ ሀገርን ከድህነት ለማውጣት እያደረጉ ያሉትን ብርቱ ጥረት ለመታዘብ ችሏል፡፡ ወጣቶቹ የተደረገላቸውን ውስን ድጋፍ ተጠቅመው ለሌሎች ምሳሌ የሆነ ተግባር በመፈፀምም አበው ‹‹ወጣት የነብር ጣት›› የሚሉትን የብርታትና የጥረት ቢሂል በተጨባጭም እያስመሰከሩ መሆኑን እኛም በተጨባጭ አረጋግጠናል፡፡ ወጣቶቹ በአግሮ ኢንዱስትሪውም ሆነ ለሀገር የውጭ ምንዛሬ ሁነኛ ምንጭ ለመሆን ላለሙት የልማት ግብ መሳካት የሚመለከተው አካል አስፈላጊውን ድጋፍ በወቅቱ እንዲያደርግላቸው ለማስገነዝብ እንወዳለን፡፡

# የምድር በረከት

# ተፈላጊነታቸው የጨመረው የሀገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ግብዓት ማዕድናት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ከተለገሰቻቸው በርካታ ማዕድናት መካከል ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውሉ ማዕድናት ይገኙበታል፡፡ እነዚህ እንደ ድንጋይ ከሰል፣ ካአሊን፣ ዶሎማይት፣ ኳርትዝ፣ ፊልድስባር፣ ዳያቶማይት፣ ቤንቶናይት ያሉት ለተለያዩ ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት የሚያገለግሉ ማዕድናት ከክምችት አኳያ ሲታዩም እንዲሁ በርካታ ናቸው፡፡

እነዚህ ማዕድናት እያሉ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሀገሪቱ ፋብሪካዎች አብዛኛዎቹን ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውሉ ማዕድናት ከውጭ ሀገር እያስመጡ ይጠቀሙ እንደነበር ይታወቃል፡፡ እነዚህ ማዕድናት ሀገር ውስጥ መመረት ከጀመሩ ወዲህ ግን በርካታ ፋብሪካዎች ፊታቸውን ወደ ሀገር ውስጥ ምርቶች መመለስ ጀምረዋል፡፡ የድንጋይ ከሰልን ለእዚህ በአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በድንጋይ ከሰል ምርት ሀገሪቱ ራሷን መቻል ጀምራለች፡፡ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች የድንጋይ ከሰልን በብዛት ይጠቀማሉ፤ የካአሊን ማዕድን፣ በውሃ ፋብሪካዎች ይፈለጋል። ኢንዱስትሪዎች እየተስፋፉ ባሉበት በዚህ ወቅት የማዕድናቱ ተፈላጊነት እየጨመረ መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

የኢንዱስትሪ ማዕድን ኮርፖሬሽንም ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት የሚውሉ ማዕድናትን ለረዥም ጊዜያት በማምረት ይታወቃል፡፡ በኮርፖሬሽኑ ከፍተኛ የማዕድን ባለሙያና የሥነ ምድር ተመራማሪ (ጂኦሎጂስት) አቶ ሳዲቅ ከቢር እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ ብዙ ዓይነት የኢንዱስትሪ ማዕድናት አሏት። ኮርፖሬሽኑ ከእነዚህ መካከል በካአሊን፣ ዶሎማይት፣ ኳርትዝ፣ ፊልድስባር፣ ዳያቶማይትና ቤንቶናይት ላይ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በአሁኑ ወቅት በኦሮሚያ ክልል ጎጂ ዞን አርዳጅላ ወረዳ ፋብሪካ በመገንባት ካአሊን የተሰኘውን የኢንዱስትሪ ማዕድን በፋብሪካ ደረጃ በማምረት ገቢ እያስገኘ ነው፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ የካአሊን ማዕድን ብዙ ጥቅሞች አሉት፡፡ በዋናነት የሀገሪቱ የውሃ የማጣራት ሥራ የሚከናወነው በዚህ ማዕድን ነው፡፡ ኮርፖሬሽኑ በሀገሪቱ ብቸኛ የካአሊን ማዕድን አምራችና አቅራቢ ሲሆን፣ ማዕድኑ ከተመረተ በኋላ አዋሽ መልካሳ አልሙኒየም ሰልፌት ለተባለ ድርጅት ይቀርባል፡፡ ይህ ድርጅትም በማዕድኑ ላይ እሴት በመጨመር ምርቱን ለመጠጥ ውሃ አምራቾች ያቀርባል፡፡

‹‹ዋናው የካአሊን ማዕድን አገልግሎት ግን የመጠጥ ውሃ ማጣራት ነው፡፡ የካአሊን ማዕድንን ማምረት ከቆመ፤ የመጠጥ ውሃም ሥራው እንደቆመ ይቆጠራል፡፡ ለዚህም ነው ኮርፖሬሽኑ ትልቅ ኃላፊነት ወስዶ በካአሊን ላይ እየሰራ የሚገኘው፡፡ ካአሊን ማዕድን ውሃን ከማጣራት በተጨማሪም ለወረቀት እና ለሴራሚክ ፋብሪካዎች ግብዓትነት ይውላል፡፡

ቀደም ሲል ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ዶሎማይት፣ ኳርትዝ፣ ፊልድስባርና፣ ታንታለም እያመረተ ያቀርብ እንደነበር አስታውሰው፤ በተለይ የታንታለምና የዶሎማይት ማዕድንን ቀንጤቻ አካባቢ ፋብሪካ ተቋቁሞ በፋብሪካ ደረጃ ይመረት እንደነበር ይናገራሉ፡፡ ታንታለም የማምረቱ ሥራ ሲቆም ዶሎማይት የማምረት ሥራ አብሮ መቆሙን ይገልፃሉ፡፡ እንደ ዶሎማይት፣ ኳርትዝና ፊልድስባር ዓይነቶቹ ማዕድናት በአነስተኛ ማህበራት ደረጃ ብቻ እንዲመረቱ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ማህበራት ተደራጅተው እንዲያመርቱ መደረጉን ያስረዳሉ፡፡

እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፤ ታንታለም የማምረቱን ሥራ እንደገና ለመጀመር እየተሰራ ነው። ታንታለም ሲመረት ኳርትዝና ፊልድስባር፣ አብሮ በማምረት እሴት በመጨመር ለገበያ ይቀርቡ ነበር። በአሁኑ ወቅትም እነዚህ ማዕድናት ለብረትና መሰል ፋብሪካዎች ግብዓት የሚውሉ ሲሆን፣ ጥሬ እቃዎቹን ከአምራቾች በመግዛት እሴት በመጨመር ለማቅረብ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡ በተመሳሳይ ካአሊን ማዕድን የሚያመርተው ፋብሪካ በማዘመን ፋብሪካው በተሻለ ደረጃ እንዲያመርትና ለተለያየ ግብዓት እንዲውሉ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሰሩ ነው፡፡ ለእዚህም የማስፋፊያ በጀት ተይዞለት እየተሰራ ነው፡፡



የካኦሊን ማዕድን ፤

በዝዋይ አካባቢ የሚገኘውን ዳያቶማይት የተሰኘ ማዕድን ለማምረትም የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማን መካሄዱን ጠቅሰው፣ ከኦሮሚያ ክልል ፈቃድ ለመወሰድ ጥያቄ እየቀረበ መሆኑንና ወደ ሥራ ለመሰማራት የሚያስችል ዝግጅት መደረጉን ይገልጻሉ።

‹‹የዳያቶማይት ማዕድን ብዙ አገልግሎቶች አሉት። ለቢራ፣ ለስላሳ እና ጁስ ፋብሪካዎች ለማጣሪያነት ይውላል፡፡ ይህ ማዕድን አሁን ከቻይና እና ከተለያዩ የውጭ ሀገራት በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ይመጣል›› ሲሉም ጠቅሰው፣ ማዕድኑን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በሀገር ውስጥ በማምረት ከውጭ የሚመጣውን ለመተካት ያለመ ሥራ እየተሰራ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ ኮርፖሬሽኑም የማምረት ፈቃዱን እንዳገኘ ወደ ማምረቱ ሥራ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

በተጨማሪም የዳያቶማይት ማዕድን ፀረ-ተባይ ኬሚካል ለማምረት እንደሚጠቅም ጠቅሰው፤ ኮርፖሬሽኑ ቀደም ባሉት ጊዜያት ይህን ማዕድን በማምረት የጸረ ተባይ ኬሚካሎችን ለሚያመርቱ ፋብሪካዎች ያቀርብ እንደነበር ያስታውሳሉ። ማዕድኑን የማምረቱ ሥራ አሁን ላይ በአነስተኛ አምራችነት ለተደራጁ ሥራ አጥ ወጣቶች መሰጠቱን ይገልጻሉ። ኮርፖሬሽኑ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ማዕድኑን በከፍተኛ ደረጃ ለማምረት የሚያስችል ሥራ እየሰራ መሆኑን ያመላክታሉ፡፡

እንደ አቶ ሳዲቅ ማብራሪያ፤ ኮርፖሬሽኑ የካአሊን ማዕድን ማምረት ከጀመረ ረዘም ያሉ ጊዜያትን ያስቆጠረና ለፋብሪካዎች እያቀረበ ያለ ነው። ምርቱንም ለአዋሽ መልካሳ የአልሙኒየም ሰልፌት ፋብሪካ ስለሚያቀርብ እሴት ተጨምሮበት ለመጠጥ ውሃ ማጣሪያነት ይውላል፡፡ አሁን ፋብሪካ በዓመት 3ሺ500 እስከ አምስት ሺ ቶን የካአሊን ማዕድን ያመርታል፡፡ ፋብሪካው ሀገር ውስጥ ያለውን ፍላጎት ለማሳካት የሚያስችል ምርቶች እያመረተ ይገኛል። በዚህ ዘርፍ 130 ሰዎች የሥራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡

አሁን ላይ ፋብሪካው የሚያመርተው የኮአሊን ምርት ለሀገር ውስጥ ገበያ በቂ ቢሆንም፣ ግብዓቱን የወረቀትና ሴራሚክ ፋብሪካዎች ከውጭ ሀገራት የሚያስመጡበት ሁኔታ ይታያል ሲሉ አመልክተዋል፡፡ ፋብሪካዎቹ የሀገር ውስጡን ምርት የማይጠቀሙበትን ምክንያት ሲያብራሩም ፋብሪካ ከአዲስ አበባ 430 ኪሎ ሜትር ርቀት መገኘቱን በሩቅነት እንደሚጠቅሱ ይገልጻሉ፡፡

በሀገሪቱ የሀገር ውስጥ ፍላጎት ማሟላት የሚችል የካአሊን ማዕድን ከፍተኛ ክምችት እንዳለም ጠቅሰው፣ ኮርፖሬሽኑ ይህን ታሳቢ በማድረግ ዘመናዊ ፋብሪካ ለመገንባት እየሰራ መሆኑን አቶ ሳዲቅ ያመለክታሉ። የዳያቶማይት ማዕድንን ከሀገር ውስጥ አልፎ ለውጭ ሀገራት ገበያ ማቅረብ የሚያስችል ከፍተኛ ክምችት እንዳለ ጠቁመዋል፡፡

እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፤ የቢራ፣ የለስላሳ ፋብሪካዎች አሁን እየተጠቀሙ ያሉትን የዳያቶማይት ማዕድን በሀገር ውስጥ ማምረት እየተቻለ ከውጭ እያስመጡ ነው፡፡ ይሁንና ፋብሪካዎቹ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ሲሉ ዳያቶማይት የዳያቶማይትን ይዘት ሲጠየቁ ለመናገር ፈቃደኛ አይደሉም ሲሉ ጠቅሰው፣ የሀገር ውስጡን ምርት አያበረታቱም ይላሉ፤ ጥቅሙን ከራሳቸው እንጂ ሀገሪቱ ከምታወጣው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ አንጻር እንደማያዩ አመልክተው፣ ከውጭ የሚመጣውን ምርት ለማስቀረት የሚደረገውን ጥረት አይደግፉም ብለዋል፡፡ ወደፊት በዳያቶማይት ማዕድናት ላይ ኮርፖሬሽኑ እየሰራ ያለውን ሥራ አጠናክሮ ማስቀጠል ከተቻለ በቂ ምርት ማምረት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

እሳቸው እንዳብራሩት፤ የካአሊን ምርት ከፍተኛውን የኮርፖሬሽኑን ገቢ የያዘ ሲሆን፤ አንድ ቶን የኮአሊን ምርት ከ13ሺ እስከ 15ሺ ብር ድረስ ይሸጣል። በዘንድሮው በጀት ዓመት 5ሺ ቶን የካአሊን ምርት ለማምረት ታቅዶ እስካሁን ከእቅድ በላይ ማምረት ተችሏል፡፡

‹‹የኢንዱስትሪ ማዕድናት ተፈላጊነት በጣም እየጨመረ ነው፡፡ ትላልቅ ፋብሪካዎች በተገነቡ ቁጥር የኢንዱስትሪ ማዕድናት ፍላጎት እየጨመረ ይመጣል›› ያሉት አቶ ሳዲቅ፤ ድሮ የማይጠየቁ (የማይፈለጉ ማዕድናት) ተፈላጊ እየሆኑ መምጣታቸው ይናገራሉ፡፡ ለእዚህም የድንጋይ ከሰል ምርት ተፈላጊነት እየጨመረ መምጣትን ለአብነት ጠቅሰዋል፡፡ የፋብሪካዎች መብዛት የኢንዱስትሪ ማዕድናት ተፈላጊነት እንዲጨምር የሚያደርግ መልካም አጋጣሚ እንደሚፈጥር ገልጸዋል። ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ማዕድናት ምርት እንደሚታወቅ ተናግረው፣ በርካታ ፋብሪካዎች ወደ ኮርፖሬሽኑ በመምጣት የሚያስፈልጋቸውን ማዕድን ታመርታላችሁ ወይ በማለት እስከመጠየቅ ደርሰዋል›› ሲሉ ያስገነዝባሉ፡፡

ኮርፖሬሽኑም የፋብሪካዎችን የማዕድን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ከሚያመርታቸው ማዕድናት በተጨማሪ የሚፈለጉ ሌሎች ማዕድናት ፍለጋ ላይ እየተሰማራ መሆኑንም አስታውቀዋል። የኢንዱስትሪዎች የማዕድናት ፍላጎት እየጨመረ በመጣ ቁጥር ኮርፖሬሽኑ የሚያመርታቸውን የማዕድናት ምርት ብዛት ለመጨመር ይሰራል ብለዋል፡፡ በተለያዩ የማዕድናት ልማቶች ላይ ለመስማራት የሚያስችሉ ሥራዎች ከወዲሁ እየሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

በኢንዱስትሪ ማዕድናት ልማቱ ላይ በርካታ ተግዳሮቶች እንደሚታዩም አቶ ሳዲቅ ጠቁመዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ ከእነዚህ ተግዳሮቶች ውስጥ አንዱ ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ማዕድናት በቀጥታ ማምረት አለመቻሉ ነው፡፡ ቀደም ሲል ማዕድናቱን ከሚያመርቱ ማህበራት ጋር ክፍተቶች ነበሩበት፤ በአሁኑ ወቅት መሻሻሎች እየታዩ ናቸው። ማዕድናቱን በማምረት ሥራ ላይ ከተሰማሩ በአነስተኛ ደረጃ ከተደራጁ ማህበራት ጋር አብሮ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ከማህበራት ጋር አብሮ መሥራት የሚያስችሉ ሁኔታዎች በመፍጠር ማህበራቱን በማገዝ፣ ለማህበራቱ ድጎማ በማድረግና በመቶኛ በማጋራት ድጋፍ እያደረገ እያመረተ ይገኛል፡፡

ኮርፖሬሽኑ ማዕድናቱን በቴክኖሎጂ በመጠቀም ማምረት የሚቻልበት ሥራ መሥራት እንደሚጠበቅበት አቶ ሳዲቅ አስታውቀዋል፤ በአሁኑ ወቅት ኢንዱስትሪዎች እየተስፋፉ መምጣት የፍላጎት መጨመሩን ከፍተኛ ደረጃ እንዳደረሰው ጠቅሰው፤ በኢንዱስትሪ ማዕድናት ላይ ብዙ መሥራት እንደሚጠበቅ ያመለክታሉ፡፡

ከገበያ አንጻርም ሲያብራሩ ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት አካሄዶ ወደ ሥራ እንደሚገባ ገልጸው፣ ፋብሪካዎቹ የሚፈልጉት የማዕድን ዓይነት ጥራትና ብዛት ከተለየ በኋላ ማዕድናቱን ወደ ማምረት እንደሚገባ ያብራራሉ፡፡ ፋብሪካዎች የሚጠይቁት የጥራት ዓይነት እንደሚለያይ አመልክተው፣ በጠየቁት የጥራት መጠን ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ እንደሚሰራም አስታውቀዋል፡፡

አቶ ሳዲቅ እንደገለጹት፤ ማዕድናት በተፈጥሮ እኩል የሆነ ጥራት የላቸውም፤ አንድ ዓይነት ማዕድን ሆኖ አንድ ቦታ ላይ ያለው ማዕድን ጥራት ፤ ሌላ ቦታ ላይ ካለው ማዕድን ጋር በጥራት ሊለያይ ይችላል። ማዕድናቱ በላቦራቶሪ ከተፈተሹ በኋላ ያላቸው ጥራት መጠን ይለያል፤ ማዕድኑ ያለው የጥራት ደረጃ ለየፋብሪካዎቹ እየገለጸ አቅርቦቱ ይፈጸማል፡፡

የማዕድናትን ጥራት ከፍ ለማድረግ ቴክኖሎጂ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው አስታውቀዋል። ሀገር ውስጥ የሚመረቱት ማዕድናት ጥራት ላይ የሚነሳው ችግር ከእጥበት ጋር የተያያዘ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከውጭ የሚመጡት ማዕድናት በቴክኖሎጂ በመጠቀም እንደሚታጠቡ ተናግረዋል፡፡ ማዕድናት እንደተመረተ ለገበያ የሚቀርቡበት ሁኔታ ጥራት ላይ ችግር እንዲኖር እንደሚያደርግ አመልክተው፣ እሴት ተጨምሮበት፣ በቴክኖሎጂ ታግዞ ከተመረተ ተፈላጊነቱ እንደሚጨምር ገልጸዋል፡፡

እሳቸው እንዳብራሩት፤ የድንጋይ ከሰል ለአብነት ቢወሰድ ሀገር ውስጥ የሚመረተው የድንጋይ ከሰል ከውጭ ያነሰ ጥራት የለውም፡፡ ከውጭ የሚመጣው ታጥቦ ስለሚመጣ የካሎሪ መጠኑ ከፍ እንዲል ያደርገዋል፡፡ አሁን ላይ ሀገር ውስጥ የድንጋይ ከሰል ማጠቢያ ፋብሪካ እየተቋቋመ ነው፤ በዚህም የድንጋይ ከሰል እየታጠበ ለፋብሪካዎች እያቀረበ ይገኛል። እንደዚህ ዓይነት ፋብሪካዎች መኖር የማዕድናት ምርቶችን የጥራት መጠን ከፍ እንዲል እንደሚያደርግ አቶ ሳዲቅ አስታውቀዋል፡፡

በቀጣይ በቴክኖሎጂ በመታገዝ በኢንዱስትሪ ማዕድናት ላይ የሚሰሩ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡ የካአሊን ፋብሪካን በማዘመን በቴክኖሎጂ የታገዘ ምርት ለማምረት የሚያስችል ሥራ ይሰራል። ድንጋይ ከሰል ማምረት ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚያስችሉ ቅድመ ዝግጅቶች እየተደረጉ ነው፡፡ እንደ ማርበል ያሉ ሌሎች የኢንዱስትሪ ማዕድናት ለማምረት ብዙ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን ነው ያስታወቁት፡፡

በአጠቃላይ ኮርፖሬሽኑ በሀገሪቱ ላይ አሉ የተባሉ ማዕድናት ላይ ለመስማራት የሚያስችሉ ሥራዎችን መሥራት ስለሚጠበቅበት በዚያ ልክ አቅምን የመገንባት የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሰሩ ነው፡፡ በማዕድኑ ዘርፍ መንግሥትም እገዛ እያደረገ ስለሆነ በኢንዱስትሪ እና በሜታሊክ ማዕድናት ዘርፍ ብዙ ሥራዎች ለመሥራት ታቅዶ፤ የሰው ኃይል በማደራጀት የአምስት ዓመት ስትራቴጂ ተቀርጾ እየተሰራ ነው፡፡

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## «የወርቅ እንቁላል»

እዩኤል ወርቁ

እዚህ ከተማ ውስጥ ጠጅን እንደ ጠንክር የሚጠጣት ሠው አለ ቢሏችሁ እንዳታምኑ፡፡ ጠጅ ራሷ ጠንክር ካልጠጣት የተጠጣችም አይመስላት፡፡ «ልብስ መስቀያውን አገኘ» እንዲሉ ጠጅም ብርሌዋን አገኘች ከተባለ ጠንክር ሰቦቃ ነው፡፡ ታድያ ጠንክር ጠጅ ብቻውን አይደለም የሚጠጣው፤ ከሳቅና ጨዋታው ጋር እንጂ፡፡

አንድ ቅዳሜ ከጋሽ ምንተስኖት ጋር ቁጭ ብለው የብርሌ አንገት ሲቆጠሩ ጋሽ ምንቴ ጠየቁ ...

«እኔ የምልህ ጠንክር፤ ለመሆኑ እኚህ ፓትርያርኩ አቡነ ጳውሎስ እህል የሚበሉ ይመስልሃል?»

«መቼስ መብላትማ ስጋ ያለ እህል፣ ነፍስ ያለ ስጋ አይቆም ይበሉ ይሆናል እንጂ፡፡ ግን ባይሆን ብፁዕ ስለሆኑ እንደ እኔና እንደ ርስዎ ሽንት ቤት አይቀመጡ ይሆናል። ቢቀመጡ እንኳን የወርቅ እንቁላል ቢጥሉ ነው፡፡» ብሎ ጠንክር ረቂቅ እውቀት ተናገረ፡፡

እንግዲህ ጋሽ ምንተስኖት «የመንደሩ አድባር» የተባለላቸው ባለሱቅ ናቸው፡፡ ታድያ የጋሽ ምንቴ ሩብ ያህል የገንዘብ ተቀማጭ ያለው በጠንክር ስም ነው፡፡

«እንዴት?» ቢሉ፣

ምስክር እንዲሆን የጠንክር የዱቤ ደብተር በሱቃቸው የገንዘብ ካዝና ውስጥ በጥንቃቄ ተቀምጦ ይገኛል፡፡ በዚህ ምክንያት ጋሽ ምንቴ ሁልጊዜ የድህነት ስጋት ላይ ናቸው። በዚያ ላይ ጠንክር በሱቃቸው በኩል ባለፈ ባገደመ ቁጥር ዛሬ እሞታለሁ፣ ነገ እሞታለሁ እያለ ያስቦካቸዋል፡፡

አንድ ቀን ግን ጠንክር ለይቶለት ጨርቁን ጥሎ አበደ። የእብደቱን ምክንያት የመንደሩ ጠቢባን አዋቂዎች ጤዛ ልሰው፣ ስራ ስር ምሰው፣ ቅጠል በጥሰው ሲመረምሩ ጠንክር በገንዘብ ማጣት የተነሳ አርባ ቀን አርባ ሌሊት ጠጅ ሳይጠጣ ከርሟል አሉ፡፡ ጊዜው የሁዳዴ ጦም በመሆኑ ሰይጣን የጠንክር ጠጅ ማቆም የጥድቅ ስራ እንጂ የገንዘብ ማጣት ስላልመሰለው አጉል ተተናኩሎት ኖሯል፡፡

ጋሽ ምንተስኖት መቼም የዋዛ ሰው አይደሉም። ዘመድ አዝማድ ሰብስበው ሲመክሩ ጠንክር ዕብደቱ ተስማምቶት ከቀጠለ የዱቤው ደብተር ለቁጭት ይቀመጣል እንጂ የገንዘባቸው ጉዳይ ውሃ እንደሚበላው ተነገራቸው፡፡ በመጨረሻ ሚስትና ልጆቻቸውን ለመንደሩ ሰው አደራ ትተው ርቀው ተሰደዱ፡፡ ጠንክርን ሶስት ሰባት አስጠምቀው ከነሙሉ ጤንነቱ ይዘውት ሲመለሱ «ሹልክ ብዬ ቅምስ» ጠጅ ቤት ጥለውት በድል አድራጊነት ወደ ቤታቸው ገቡ። ያን ቀን ማታ ሚስታቸው እትዬ ምንተስኖሽ የጀግና አቀባበል አደረገችላቸውና እንዴት ያለ ሌሊት አለፈ፡፡ አይ ሌሊት፣ ሌሊት ብሎ ዝም ነው!

«ምናለ ለኔ ሲል አስራ ሶስት ወር ሌሊት በምድሪቱ ላይ በነገሰ። ያኔ ነበር የአስራ ሶስት ወር ፀጋ እያሉ መሸለል» አሉ በማግስቱ ለጋሽ ደጀኔ ሲያወሯቸው፡፡ እንግዲህ ጋሽ ደጀኔ ስልብ መሆናቸውን ልብ ይሏል፡፡

ጠንክር በጋሽ ምንቴ ታጋይነት እብደቱን በሶስት ሰንበት ጠበል ድል ነስቶ ከተመለሰ በኋላ ግን እርምም ሳይቆይ ሞት ያሳድደው ጀመር፡፡ ለጋሽ ምንቴ ሲነግራቸው በመጀመሪያ የተለመደው ቀልድ መስሏቸው...

«የምንተስኖትን ብድር ሳትከፍል እሞታለሁ ማለት ዘበት ነው፡፡ ብትሞት እንኳን መቃብር ፈንቅየ አወጣሃለሁ» ብለው ቀለዱበት፡፡

ኋላ ግን ነገሩ ሲደጋገም እውነትም ሞት የጠንክር አፍንጫ ስር እያነፈነፈ መሆኑን ተረዱ፡፡ በዚህ ጊዜ የአፍላነት ጀብደኝነታቸው ሽው አለባቸውና ...

«የማን ወንድ ነው ጫፍህን ንክት የሚያደርግህ?» ብለው ሸለሉ፡፡

«ኧረ የዘንድሮስ ቁርጥ ነው ጋሽ ምንቴ፣ ሞቱማ በነፍስ ነው የሚፈልገኝ፡፡» አላቸው፡፡

አንድ ሰሞን ጥበቃው አስቸገራቸው፡፡ ሱቃቸውን ጥርቅም አድርገው ዘግተው ጠንክር በወጣ በገባበት፣ ባለፈ ባገደመበት ሁሉ እየተከተሉ ሲጠብቁት ሰነበቱ፡፡ ኋላ ግን በአንድ በኩል ሞቱንማ በቀላሉ ታግለው የማይጥሉት ጠላት መሆኑ ሲገባቸው፣ በሌላ በኩል ጥበቃው ምርር ሲላቸው ጊዜ ጠንክር ገና በህይወት እያለ ብድሩን ከፍሎ ካለጨረሰ ሲሞት ልብና ኩላሊቱን የመውረስ መብት እንዲሰጣቸው የከተማውን ማዘጋጃ ቤት በማመልከቻ ጠየቁ፡፡

ማዘጋጃ ቤቱም በከተማው ውስጥ በተፈጠረው የመቃብር ቦታ እጥረት የተነሳ ጋሽ ምንቴ አስከሬኑን ጓሯቸው የሚቀብሩ ከሆነ አይደለም ልብና ኩላሊቱን፤ አይኑና ጆሮውን፣ እጅና እግሩን፣ ሳንባና ፈርሱን ሳይቀር የመውሰድ እና ለውሻቸው ከመስጠት ጀምሮ ለፈለጉት አላማ ማዋል እንደሚችሉ አስረግጦ ቃል ገባላቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ጋሽ ምንተስኖት ህይወታቸው የተረጋጋና የሰከነ ሆነ፡፡ ታድያ ይሄ ወሬ በከተማው ሲነዛ ሁሉም ሰው የገረመው አንድ ነገር፣ ለካ ጠንክርን እንደ ሰው መንግሥት ያውቀዋል የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ይሄንን ሞት ግጦ የተፋው የሰው ጡር ማን በከተማው ማዘጋጃ ቤት ውስጥ ስሙ በመዝገብ ሰፍሮ ይገኛል ብሎ ገመተ፡፡

«ዘመን ዘመንን እየወለደ» እንዲሉ ከጋሽ ምንተስኖት እና ከከተማው ማዘጋጃ ቤት ፊርማ በኋላ እንደ ዘበት ዓመታት ተቆጠሩ፡፡ ጋሽ ምንቴ ከጠንክር እዳ ይልቅ ልብና ኩላሊቱ ቢሸጥ የበለጠ ዋጋ እንደሚያወጣላቸው አምነዋልና የጠንክር ሞት እንደ ምፅአት ቀን ራቀባቸው፡፡ ከጎጃም ደብተራ ጀምረው እስከ ወሎ ቃልቻ ድረስ በመተተኛ ቢያስደግሙ፣ ጠጠር ቢያስጥሉ፣ ሞራ ቢያስነብቡ ወይ ፍንክች ጠንክር የአባ ቢላዋ ልጅ፡፡ ጭራሽ እድሜው እንደ አብርሃም ረዘመ፡፡ ጡር ካልፈራ ክርስቶስ ዳግም ለፍርድ እስኪመጣ ድረስ ጠጅ እየጠጣ ሳይጠብቀውም አይቀር፡፡

ታድያ በዚህ ሁሉ መሃል ጋሽ ምንቴ ያልተገለጠላቸው አንድ የተፈጥሮ ረቂቅ ምስጢር ነበር፡፡ ለካ ባለ እዳው ጠንክር ብቻ ሳይሆን ቀጠሮ ቀናቸው ከደረሰ እርሳቸው ራሳቸው ቀድመው ሊጠናቀቁም ይችላሉ፡፡ ግን ጋሽ ምንቴ ይሄ ረቂቅ የተፈጥሮ ምስጢር ሲገባቸው በጣም ዘግይተው ኖሯል፡፡

አንድ ምሽት ከጋሽ ደጀኔ ጋር ጠጅ ሲጠጡ ቆይተው ለሽንት ቀዬ በተዛወሩበት እብድ ውሻ ነከሳቸው፡፡ ከጠንክር ቀድመው አበዱ፣ ከጠንክር ቀድመው ተፈጠሙ!

እንግዲህ ጋሽ ምንቴ በህይወት እያሉ የትም በከንቱ በትነው ሳይሰበስቡት ስለቀረባቸው ጥሪት ሲያሰላስሉ ንስሃ መግባቱንም ዘንግተውት ሞት ደርሶ አይናቸውን ከደነ፡፡

አንድ ቀን ታድያ ስልቡ ጋሽ ደጀኔ ሞተው ቤተ-ዘመድ ቀብሯቸው በተመለሰ በሶስተኛው ቀን አፈራቸውን አራግፈው ተነሱ፡፡ ኋላ «ሹልክ ብዬ ቅምስ» ጠጅ ቤት ቁጭ ብለው በላይኛው ሀገር ስላዩአቸው ተዓምራት ሲያወሩ ጋሽ ምንቴን በገነት ምን የመሰለ ሱቅ ከፍተው ገበያቸው ደርቶ እንዳገኟቸው ተናገሩ፡፡

የጋሽ ምንቴ ገነት የመግባት ጉዳይ እንቆቅልሹ ቢመረመር፣ ቢብጠረጠር ማን ሊቅ ማን ረቂቅ ይፍታው። አንድ ቀን ጠንክር በስካር ምስጢሩን ይፋ እስኪያወጣው ድረስ፡፡

ጋሽ ምንቴ በተቀበሩ በሶስተኛው ቀን የትንሳኤ መለከት ከመነፋቱ ቀደም ብሎ እኒያ አቡነ ጳውሎስ ለጉዳያቸው ወደ ጓሮ ዞሩ አሉ፡፡ በዚያም የጋሽ ምንቴ ትኩስ የመቃብር አፈር ሸተታቸው፡፡ እንግዲህ ምን ቅን መልዓክ እንዳማከራቸው እንጃ እንደ ጃንሜዳ ከተንጣለለው የሙታን ሀገር መካከል መርጠው የጋሽ ምንቴ መቃብር ላይ የወርቅ እንቁላላቸውን ጣሉ፡፡ የጋሽ ምንቴ ትኩስ የመቃብር አፈር ላይ ያረፈው የወርቅ እንቁላል ወዙ ከአፈሩ አልፎ፣ ገላቸውን ዘልቆ ነፍሳቸውን አረጠባትና እነሆ በመንግስተ ሰማይ ሱቃቸውን ከፈቱ፡፡

አሁንም ጠንክር ሲመጣ እዳየን ይከፍለኛል የሚል ተስፋ አላቸው ይባላል፡፡

«ችርስ ለአቡናችን የወርቅ እንቁላል!» አለ ጠንክር ብርሌውን ከፍ አድርጎ።

# ዓለም አቀፍ

## የኤምሬትስ ፕሬዚዳንት በጋዛ የአስቸኳይ ተኩስ አቁም እንዲደረስ ጠየቁ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በቤጂንግ ትናንት የተጀመረው የቻይና አረብ የትብብር ጉባኤም ዋነኛ አጀንዳው የጋዛ ጦርነት ሆኗል።

በጉባኤው ንግግር ያደረጉት የአረብ ኤምሬትሱ ፕሬዚዳንት ሼክ መሀመድ ቢን ዛይድ፤ “የቻይና እና አረብ ሀገራት መሪዎች ስብሰባ ዓለም ለተጋረጡባት ፈተናዎች የጋራ መፍትሔ በምትሻበት ወቅት እየተካሄደ ነው” ብለዋል።

በጋዛ ሰርጥ እየተካሄደ ያለው ጦርነት የመካከለኛው ምሥራቅ ውጥረት ይበልጥ ማባባሱን በመጥቀስም ጦርነቱ አሳሳቢ የሰብአዊ ቀውስ ማስከተሉን አብራርተዋል።

የንጹሃንን ህይወት እየቀጠፈ የሚገኘውን ጦርነት ለማስቆም የቤጂንግ እና የአረብ ሀገራት ትብብር ወሳኝ መሆኑንም ተናግረዋል።

በጋዛ ተኩስ ቆሞ የሰብአዊ ድጋፎች በፍጥነት እንዲደርሱ ብሎም ዘላቂ ሰላም ሰፍኖ የሁለቱ መንግሥታት መፍትሔ ተግባራዊ እንዲሆን የተቀናጀ ሥራ መሥራት እንደሚገባም ነው ፕሬዚዳንቱ ያነሱት።



ሼክ መሀመድ ቢን ዛይድ ፣

የቻይናው ፕሬዚዳንት ሺ ጂንፒንግ በበኩላቸው፤ “የፍልስጤማውያንን ሰቆቃ ያበዛው ጦርነት መቋጫው ሳይታወቅ ሊቀጥል አይጋባም” ብለዋል። ፕሬዚዳንቱ የፍልስጤም ሉአላዊ ሀገርነት እንዲረጋገጥም ጥሪ አቅርበዋል።

“የሁለት መንግሥታት መፍትሄ”ን የምትደግፈው ቤጂንግ በጋዛ ለሰብአዊ ድጋፍ የሚውል 500 ሚሊዮን ዩዋን (69 ሚሊዮን ዶላር) ለመስጠት ቃል የገባች ሲሆን፤ በመንግሥታቱ ድርጅት ተቋማት በኩል ድጋፍ ለመላክም 3 ሚሊዮን ዶላር መመደቧ ተገልጿል።

ቻይና የእስራኤልና ሃማስ ጦርነት ከተጀመረ አንስቶ ለፍልስጤማውያን ድጋፍ ስትሰጥ እስራኤልን ስትቃወም መቆየቷ ይታወሳል።

የቤጂንግን አቋም የሚጋሩት የአረብ ሀገራት በፈረንጆቹ 2004 የመሠረቱት የቻይና አረብ የትብብር ፎረም በቤጂንግ ሲጀመር የግብጽ፣ ባህሬን እና ቱኒዚያ መሪዎችም እየተሳተፉ ነው።

ጉባኤው ከጋዛ ጉዳይ ባሻገር የአረብ ሀገራት እና ቤጂንግን የንግድ ትስስር በሚያሳድጉ ጉዳዮች ላይ እንደሚመክርም ይጠበቃል።

## በሳርክ ደሴት የምትገኘው የዓለማችን ጠባቧ እስር ቤት

በእንግሊዝና ፈረንሳይ መካከል የምትገኘው ሳርክ ደሴት የዓለማችን ጠባቧ እስር ቤት ትገኛለች።

አምስት ኪሎ ሜትር ርዝመትና አንድ ነጥብ ስድስት ኪሎ ሜትር ስፋት ያላት ጠባብ ደሴት መኪናም ሆነ አስፋልት መንገድ የላትም።

600 የማይሞላ ሕዝብ በሚኖርባት ደሴት እስር ቤት በመገንባት ግን ከቀዳሚዎቹ ተርታ ትሰለፋለች። በፈረንጆቹ 1856 የተሰራችው ጠባብ እስር ቤት አሁንም ድረስ ማገልገሏን መቀጠሏን ኦዲቲ ሴንትራል አስነብቧል።


እስር ቤቷ ሁለት ክፍል ያላት ሲሆን፤ ስፋታቸው አራት ካሬ እንኳን አይሞላም። በውስጣቸው አነስተኛ የእንጨት አልጋ ብቻ የሚገኝባቸው ክፍሎች ውስጥ የሚታሰሩ ሰዎች ለሁለት ቀናት ብቻ ነው የሚቆዩት።

መስኮት በሌላቸው ጠባብ ክፍሎች ለሁለት ቀናት የቆዩ ታራሚዎች ወደ ሳርክ ጎረቤት ጉርነሲ ደሴት ትልቅ ማረሚያ ቤት ይዘዋወራሉ ተብሏል።

እ.አ.አ. በ1832 በሳርክ ደሴት እስር ቤት ለመገንባት ሲታቀድ ባለሁለት ጠባብ ክፍሎቹን ለመስራት አልነበረም የሚለው የጉርነሲ ደሴት ድረገጽ በወቅቱ የገጠመው የበጀት እጥረት የዓለማችን ጠባቧ እስር ቤት እንድትገነባ ማድረጉን አውስቷል።

አስደናቂው ነገር እስር ቤቷ ባለፉት 168 ዓመታት አገልግሎት እየሰጠች መቀጠሏ ነው።

የዓለም ድንቃድንቅ መዝገብም በሳርክ ደሴት የምትገኘውን ባለሁለት ክፍል እስር ቤት “የዓለማችን ጠባቧ እስር ቤት” ብሎ መዝግቧታል።



ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# ጋብቻ በሐረሪ ብሔረሰብ

**ዳግም ከበደ**

ኢትዮጵያ በርካታ ባሕላዊ እሴቶች ያሏት ሀገር ነች። እነዚህ እሴቶች የማህበረሰቡ መገለጫ ከመሆን አልፈው በቱሪስቶች ተመራጭ መስህቦች ናቸው። ከሁሉም በላይ ግን ባሕሉን፣ ወጉንና ማንነቱን ጠብቆ ለሚኖር የህገሬው ሰው የኑሮ ዘይቤንና ራሱን የሚገልጽባቸው ሀብቶቹ ናቸው።

ማህበረሰቡ ካሉት አያሌ ባሕላዊ እሴቶች ውስጥ ቤተሰብ የሚመሰርትበትና ማህበራዊ ሕይወቱን ጠብቆ የሚያቆይበት የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ይጠቀሳል። በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ቁጥር ያላቸው ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንደመኖራቸው መጠን የጋብቻ ሥነ ሥርዓትና ባሕላዊ አንድምታዎቹም እንዲሁ ይለያያሉ።

ትዳር ለመመስረት ከመተጫጨት፣ እስከ ጋብቻ ጥያቄና ሽምግልና እንዲሁም የሠርግ ሥርዓት ድረስ የሚኖረው ሰንሰለት እንደባሕልና እንደየህገሬው ወግ ልዩነት አለው። ይህ መሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዝሀ ባሕልና እሴት እንዲኖር አስችሏል። ይህንን ሀብት መጠበቅ እሴቶቹን በቀሪው ዓለም ከማስተዋወቅ ባሻገር የቱሪዝም ሀብት ምንጭ እንዲሆኑ ማድረግ ላይም መሥራት ይገባል።

የዝግጅት ክፍላችን በዛሬው ሀገርኛ አምድ በቅርቡ በዩኔስኮ በዓለም የማይዳሰስ ባሕላዊ ሀብትነት የተመዘገበው የሸዋል ኢድ ባህል ባለቤት ወደ የሆነችውን የሐረሪ ክልል ማህበረሰብ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት እንዳስሳለን። ለዚህም የሐረሪ ክልል የባህል፣ ቅርስና ቱሪዝም ቢሮ አማካኝነት ‹‹የሐረሪ ብሔረሰብ የማይዳሰሱ ቅርሶች፣ ክንዋኔዎችና ሃይማኖታዊ፣ ባሕላዊ፣ ማህበራዊ ሥነ ሥርዓቶች›› በሚል በአቶ ገዛኸኝ ግርማ እና ቀለሟ መኮንን አዘጋጅነት የተጠናከረውን ጥናታዊ ጸሑፍ መሠረት አድርጎ ያዘጋጀውን የብሔረሰቡን የጋብቻ ባሕል እናስቃኛለን፡፡

አቶ ተወልዳ አብዶሽ የሐረሪ ክልል የባህል፣ ቅርስና ቱሪዝም ቢሮ ዳይሬክተር ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ ጋብቻ በሁለት የተለያዩ ወይም ተቃራኒ ፆታዎች መካከል በፍቃደኝነት ሕይወትን በጋራ ለመምራት የሚፈጸም በውል ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ከመሆኑም በላይ የቤተሰብ መሠረትና የኅብረተሰብ እድገት ዋስትና ነው፡፡ የሐረሪ ብሔረሰብ የጋብቻ ሥርዓትም የዚሁ ውጤት ነው። ዳይሬክተሩ ባደረሱን መረጃ መሠረትም ማህበረሰቡ በሚከተለው ባሕላዊ ክንዋኔ መሠረት ጋብቻው የሚፈጸምባቸውን የተለያዩ ሥርዓቶችን ይዘን ቀርበናል።

## የመተጫጫ መንገድ

በሐረሪ ብሔረሰብ የተለያዩ የመተጫጫ መንገዶች ያሉ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ አንዱና ዋናው የሸዋል ኢድ ቀን እንደሆነ ይነገራል፡፡ የሸዋል ኢድ በዓል ለብሔረሰቡ ወጣት ወንዶችና ልጃገረዶች የመተጫጫ መድረክ ሆኖ ያገለግላል፡፡ የሸዋል ኢድ በዓል ዕለት ወጣት ወንዶች ቀልባቸው ያረፈባትን ልጃገረድ ለትዳር የሚመርጡበት ዕለት ነው፡፡

በዚህም ምክንያት በሸዋል ኢድ በዓል ልጃገረዶች (ጌይ ወሐቻች) ከምንጊዜውም በላይ አምረው፣ ተውበውና ደምቀው ይታያሉ፡፡ የታጨች ልጃገረድ የታጨችበትን ‹‹ ኩሻ ቡሩቅ›› የተባለ ባሕላዊ ቀሚስ ትለብሳለች፡፡

ጸጉሯን ደግሞ ‹‹ገማሪ›› በመባል የሚታወቀውን ባሕላዊ የጸጉር ስሬት በመሰራት ትለያለች፡፡ በዚህ መልኩ አለባበሳቸውን ካሳመሩና ባላቸው አቅም አጊጠው፣ ተውበውና ተሽቀርቅረው ከጨረሱ በኋላ በሙጋድ (በቡድን) በመሆን ወደ ክብረ በዓሉ ያመራሉ፡፡

ወጣት ወንዶችም በተመሳሳይ ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን የወደፊት የትዳር አጋራቸውን ለመምረጥ ወደ በዓሉ በመሄድ ይታደማሉ፡፡ በሸዋል ኢድ በዓል የእጮኛ አመራረጥ ሂደት በሁለት መልኩ የሚከናወን ነው፡፡ የመጀመሪያው በዓሉ በሚከበርበት ‹‹አው ሹሉም አሕመድ›› እና ‹‹አው አቅበራ አዋቾች›› ላይ ጨዋታውን ለመመልከት ከሚመጡ ልጃገረዶች መካከል ዓይናቸው ያረፈባትን በመምረጥ ነው፡፡

ሁለተኛው የእጮኛ አመራረጥ ሥርዓት የሚፈጸመው በዓሉ የሚከበርባቸውን ሁለት ቦታዎች በቀጥታ የሚያገናኝ ‹‹አሚር ኡጋ›› (የሐረር ኢሚሬት መሪ ወይም አሚር) መንገድ ላይ ነው፡፡

**በሽምግልና የሚላኩትም ሴት አያት፣ እናት አልያም አክስት ወይም ከቤተሰቡ ከፍ ያለ ዕድሜ ያላቸው ሴት ይሆናሉ**

ልጃገረዶችም ሆኑ ወጣት ወንዶች በዚህ ‹‹በአሚር ኡጋ›› የጨዋታውን ድምቀት እየተከታተሉ በተደጋጋሚ የሚመላለሱ በመሆኑ ወንዶች አመቺ ቦታ በመምረጥ ከሚመላለሱ ልጃገረዶች መካከል ዓይናቸው ውስጥ የገባችውን ወይም የወደዷትን የሚመርጡበትና የሚያጩበት ሂደት ነው፡፡

ወጣት ወንዶች በዚህ መልኩ ቀልባቸው ያረፈባትን ወይም የመረጧትን ልጃገረድ የራሳቸው ለማድረግ ይመኛሉ፡፡ በመመኘት ብቻ ሳይቀሩ ልጅቷ የማን ልጅ እንደሆነች እስከማጠያየቅ ይደርሳሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ማወቅ ካልቻሉ ወደቤታቸው ሲሄዱ ተከታትለው የማን ልጅ እንደሆነች ያጣራሉ፡፡

በሐረሪዎች በሸዋል ኢድ የበዓል ቀን ተያይቶ፣ ተመራርጦና ተዋውቆ ለጋብቻ መብቃት ዛሬም ህያው የሆነ የብሔረሰቡ ትልቅ እሴት ሲሆን፣ በዚህ ዕለት በበዓሉ ላይ መሳተፍ ያልቻለ ወይም ያልተገኘ ወጣት እንዲሁም በበዓሉ ላይ ቢሳተፍም ዓይን አዋጅ ሆኖበት እጮኛ ሳይመርጥ የቀረ እና ያልተሳካለትን ወጣት ጓደኞቹ ‹‹ሹዋሊድ አመለጤኽ›› ይሉታል፡፡ ይህም ማለት የማታ ማታ የበዓሉ ድምቀት አሞኝቶህ ሳትመርጥ ቀረህ እንደማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል በበዓሉ ላይ ተገኝቶ መምረጥ የቻለ እና የተሳካለት ወጣት ደግሞ ‹‹ሹዋሊድ ማረኼኝ›› እንደሚባል ወይዘሮ ኑሪያ ይገልጻሉ፡፡

## ሽምግልና (የጋብቻ ጥያቄ)

በሸዋል ኢድ በዓል ዕለት የተሳካለት ወጣት ወደ ቤቱ ሲመለስ ለቤተሰቦቹ ስለወደዳት ልጅ በመግለጽ የአቶ እገሌን ልጅ የትዳር አጋሬ እንድትሆነኝ መርጫለሁና ሽማግሌ ላኩልኝ በማለት ጥያቄውን ያቀርባል፡፡ የወንዱም ቤተሰቦች በልጃቸው ምርጫ ከተስማሙ ጥያቄውን ይቀበላሉ፡፡ ካልተስማሙ ግን ራሳቸው ሌላ ያጩለታል፡፡

የልጁ ቤተሰቦች የልጅቷን ቤተሰቦች ማንነትና ሰብዕና ካጣሩ በኋላ እና በልጃቸው ምርጫ ከተስማሙ ልጅቱ ቤተሰብ ጋር ሽማግሌ ይልካሉ፡፡ በሽምግልና የሚላኩትም ሴት አያት፣ እናት አልያም አክስት ወይም ከቤተሰቡ ከፍ ያለ ዕድሜ ያላቸው ሴት ይሆናሉ። እነሱም ዛሬ እናንተ ጋር መጥተናል ሲሉ ‹‹ርኸቡ›› (የመጣችሁበትን ጉዳይ አግኙ) ይባላሉ፡፡ ቤት ገብተው ‹‹ገበቲ ኤሔር›› መደባ ላይ ይቀመጣሉ፡፡ ለጥያቄው የሚኬደው በጠዋት ሲሆን ከቀናት በተለይ ሐሙስ እና ሰኞ ይመረጣሉ፡፡ ሌሎች ቀናት ገዳቸው ጥሩ አይደለም ተብለው ይታመናል፡፡

የልጅቷ እናትና ቤተሰብም በሽማግሌዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የረጅም ጊዜ ቀጠሮ ይሰጣሉ፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት ከዘመድ ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ለመምከር እና የልጁን ቤተሰቦች ማንነት እንዲሁም ስለ ልጁም ፀባይና ስለ ሥራው ክትትል ለማድረግ እና ለማጥናት ነው፡፡

የልጅቱ ቤተሰቦች ጋብቻውን ካልፈለጉት ‹‹አፍ ወጤና›› (ሌላ ሰው ቀድሟችኋል) ይሏቸዋል፡፡ ጋብቻውን ከፈለጉት ግን በቀጠሮው ቀን ሽማግሌዎች ጫት ይዘው እንዲመጡ ሌላ ቀጠሮ ይሰጧቸዋል፡፡ ይህም የጋብቻ ጥያቄ ያቀረበውን ወጣት ለልጃቸው የፈቀዱለት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ቀነ ቀጠሮውም ሲደርስ የሙሽራው እናትና ሌሎች ሁለት ሴቶች የመተጫጫ የሐረሪ ጥቅል (ኩሻ ጫት) እና ብር ይዘው ወደ ልጅቱ ወላጆች ቤት ሲደርሱ ከልጅቷ ቤተሰቦች ሴቶች በአክብሮት ይቀበሏቸውና ሻይ ቁጢ (ከቡና ቅጠል የተዘጋጀ ሻይ) ይጋብዟቸዋል። የልጁ ቤተሰብ ያመጡትን ጫት ሽማግሌዎቹና የልጅቱ ቤተሰቦች የምርቃት ሥነ-ሥርዓት አድርገው ይፈቱና በቅድሚያ ለሽማግሌዎቹ ቀጥሎም ቤት ውስጥ ለተሰበሰቡት ለልጅቱ ዘመዶች ሁለት ሁለት እግር ጫት ይታደላል፡፡

የልጅቷንመታጨት ለማብሰር ቤት ላልመጡትም የልጅቱ ዘመድ አዝማድ ጫት ይላክላቸዋል፡፡ ጫት ያልተላከላቸው የልጅቷ ዘመዶች ተቀይመው በሠርጉ ሥነ-ሥርዓት ላይ ላይገኙ ስለሚችሉ በተቻለ መጠን ጫቱን ለሁሉም ለማዳረስ ጥረት ይደረጋል፡፡

በሀረሪዎች ጫት ከፍተኛ ቦታ ይሰጠዋል። ለምሳሌም በጋብቻ ወቅት የልጁ ቤተሰብ ጥያቄ ተቀባይነት ሲያገኝ ለልጅቱ ቤተሰቦች ተይዞ የሚኬድ መሆኑ አንዱ ሲሆን ይህም የኩሻ ጫት ይባላል። ይህ በወንዱ ቤተሰብ የሚቀርበው የኩሻ ጫት የልጅቷ ቤተሰብም የራሳቸውን ጫት አክለውበት የፍጥምጥሙን ሥነ-ሥርዓት ለማስፈጸም ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ይህ የኩሻ ጫት ሥርዓት ፍፃሜ ካገኘ የጋብቻ ጥያቄው ዕውቅና ያለው መላ ቤተሰብ ዘመድና ጎረቤት ያወቀው ይሆናል፡፡

የጋብቻ ውሉን ማሰሪያው ቁልፍ ጉዳይ ባል ለሚስቱ የሚሰጠውን ሀብት (ማህሪ) እንደ እርሻ መሬት፣ ገንዘብና ዕቃ በጋብቻው ወቅት በዝርዝር ማስፈር ይጠበቃል፡፡

## የሠርግ ሥነ-ሥርዓት

የሠርጉ ቀን እንደተወሰነ በሁለቱም ቤተሰብ በኩል የድግስ ዝግጅት ይጀመራል፡፡ የሠርጉ ቀን ከመድረሱ በፊት የልጁ ጓደኞችና ዘመዶች ለሠርጉ ለማገዶ የሚሆን እንጨት ከኤረር ወንዝ በመስበር በአህያ ጭነው ለልጅቱ ቤተሰብ ያቀርባሉ፡፡ ይህም ‹‹የዘገን›› (የቀለበት ሥነ-ሥርዓት) እንጨት ይባላል፡ ፡ የልጅቱ ቤተሰብም እንጨቱን ከተቀበሉ በኋላ ምላሹን በአንድ ቅል ወተት፤ በሌላኛው ቅል ደግሞ ብርዝ እንዲሁም አራት እስር ነጭ ሸንኩርት በሁለት ልጃገረዶች አስይዘው ወደ ልጁ ቤት ይልካሉ፡፡ ወተቱ፣ ብርዙና ነጭ ሽንኩርቱ በኤረር ወንዝ ሄደው እንጨቱን ላመጡት ወጣቶች ከወባ ለመከላከል ታስቦ የሚሰጥ ነው፡፡

የሠርጉ ቀን ሲደርስ ሙሽሮችና ቤተሰቦቻቸው ወዳጅ ዘመድ በሠርጉ ዕለት እንዲገኙላቸው ጥሪ ያደርጋሉ፡፡ ጥሪ በማድረጉ በኩል ግን ቀድሞ የሚጀምረው የሙሽራዋ ቤተሰብ ነው፡፡ ከሠርጉ ጥሪ በፊት ግን ሙሽራዋ ጓደኞቿን፣ ዘመዶቿንና ጎረቤቶቿን በየቤታቸው እየሄደች ‹‹ሚጫጩዊ›› (ነገ ልብስ እናጥባለን) ብላ ትጠራለች፡፡ በነጋታውም የተጠሩት በሙሉ የቤተሰቦቻቸውን ልብስና የሙሽራዋን ቤተሰብ ልብስ ጨምረው በመያዝ ወንዝ በመውረድ ልብሱን አጥበው እስኪጨርሱ እየተቀባበሉ ይዘፍናሉ። በዘፈናቸውም ሙሽራዋ ከእንግዲህ ከጓደኞቿ መለያየቷን፣ እንደበፊቱ ከነሱ ጋር ልብስ ለማጠብ ወንዝ መሄድ እንደማትችል የሚገልጽ ነው፡፡

ሙሽራውም በየቤቱ እየዞረ ጓደኞቹን፣ ዘመዶቹንና ጎረቤቶቹን ይጠራል፡፡ ልጃገረዶችን በእህቱ አልያም በዘመዶቹ ወይም በጎረቤት አማካይነት ያስጠራል። ወላጆቻቸውም በመልዕክተኛ ዘመዶቻቸውን፣ ዕድርተኞቻቸውንና ጓደኞቻቸውን ያስጠራሉ፡፡

## የሠርጉ ዕለት

የሠርጉ ዕለት እሁድ ቀን ሙሽራው ቤተሰብ ቤት የተጠሩት እድምተኞች እስከ ቀኑ ስድስት ሰዓት መውሉድ (የነብዩ መሀመድ /ሰ.ዐ.ወ) ከመወለዳቸው ጀምሮ ያለው ይቀራል፡፡ ይህ በወንዶች አፎቻ አማካኝነት የሚከናወን ነው፡፡ ከዚህ ሥነ-ሥርዓት በኋላ ለሠርጉ ሥነ-ሥርዓት የተዘጋጀው ምግብ ይቀርባል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሙሽራዋ ቤትም እንዲሁ ይደረጋል ።

የሙሽራው ሚዜዎች ከሙሽራው ቤት ቀለበት ስለመምጣቱ እንደ ምልክት ተደርጎ የሚወሰደውን ጥጃ ወደ ሙሽሪት ቤት ይዘው ይመጣሉ፡፡ የሙሽሪት እናት የሙሽራዋ ቀለበት ሲደርሳቸው ጥጃዋን ሊጥ ይቀቧታል፡፡ ቀለበቱ መድረሱን ካረጋገጠች በኋላ ሙሽሪት ምሳዋን መብላት ትጀምራለች፡፡ ከዚህ ሥነ-ሥርዓት በኋላ ጥጃው ወደ ሙሽሮች ቤት የሚመለስ ነው፡፡

የሙሽራው አባትም ከዘመዶቻቸውና ጓደኞቻቸው ጋር ወደ ሙሽራዋ ቤት በመሄድ በግቢው በስተቀኝ በኩል በተነጠፈው ምንጣፍ ላይ ይቀመጣሉ። የሙሽሪት አባትም እና የተወሰኑ ጓደኞቻቸውና ዘመዶች ደግሞ በስተግራ በኩል በተዘረጋው ስጋጃ ላይ በመቀመጥ የሙሽራው ሚዜዎችና ጓደኞች ሙሽሪትን ይዘው ወደ ሙሽራው ቤት እስኪሄዱ ድረስ ያለውን ሥነ-ሥርዓት ይከታተላሉ፡፡

ከዚያም ብዙ ደጅ የጠኑት የሙሽራው ሚዜዎች ሙሽሪትን እንዲወስዱ ሲፈቀድላቸው በቅሎ ይዘው ሙሽሪት ቤት ይገባሉ፡፡ በባሕሉም መሠረት የሙሽራዋ ወንድም ሙሽሪትን በቅሎ ላይ እንዲያስቀምጣት ይደረግና ጃንጥላ ከእራሷ ላይ ተይዞላትና በወንድሟ ተደግፋ ወንዶች ከበቅሎው ፊት ባሕላዊ ዘፈን እየዘፈኑና እየጨፈሩ ልጃገረዶች ከበቅሎው በስተኋላ በመሆን እየዘፈኑ ወደ ሙሽራው ቤት ይዘዋት ይሄዳሉ።

ከዚያም ሙሽሮች ወደተዘጋጀላቸው ‹‹አሩዝ›› (ጫጉላ ቤት) ይገባሉ፡፡ በዚህ መልኩ ሌሎች ተጨማሪ ሥነ ሥርዓቶች እየተካሄዱ የጋብቻ ሥነ ሥርዓቱ ይፈፀማል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# ዓርብ ስፖርት



ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## የሠራተኛው የበጋ ወራት ውድድሮች በወሳኝ ምዕራፍ

**ቦጋለ አበበ**

ጥር 19/2016 ዓ.ም በኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ የተጀመረው የሠራተኛው የበጋ ወራት ውድድር ባለፉት ወራት በተለያዩ ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ሲካሄዱ ቆይተው ወደ ወሳኝ ምዕራፍ ተሸጋግረዋል፡፡

በኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበር ኮንፌዴሬሽን(ኢሠማኮ) አዘጋጅነት የሚካሄዱት እነዚህ ውድድሮች በመጪው ሰኔ ወር ይጠናቀቃሉ ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች የሚደረጉ ፉክክሮችም ወደ ፍፃሜ እያመሩ ይገኛሉ።

በሁለት ዲቪዚዮን ተከፍሎ በሚካሄደውና ጠንካራ ፉክክር በሚያስተናግደው እግር ኳስ በሁለተኛ ዲቪዚዮን ሲካሄዱ የቆዩ ጨዋታዎች ተገባደዋል፡፡ በዚህ ዲቪዚዮን የፍፃሜ ተፋላሚ የሆኑ ሁለት ክለቦችም ባለፈው ሳምንት የግማሽ ፍፃሜ ጨዋታቸውን አድርገው ተለይተዋል፡፡ በዚህም ቃሊቲ ብረታ ብረት ፋብሪካ አዋሽ ወይን ፋብሪካን በግማሽ ፍፃሜው ፍሊሚያ 3ለ1 በመርታት የዋንጫ ተፋላሚ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ በተመሳሳይ ጠንካራ ፉክክር በተደረገበት የግማሽ ፍፃሜ ጨዋታ ኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ ኮካ ኮላ ሞኤንኮ ኩባንያ ጋር በመለያ ምት 10 ለ 9 አሸንፎ ወደ ዋንጫ ያለፈ ቡድን ሆኗል፡፡ በውድድሩ ፍፃሜም ቃሊቲ ብረታ ብረትና ኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ የሁለተኛ ዲቪዚዮን ዋንጫን ለማንሳት የሚፋለሙ ይሆናል፡፡ በግማሽ ፍፃሜው የተሸነፉት አዋሽ ወይን ፋብሪካና ሞኤንኮ ኩባንያ ደግሞ በመጪው እሁድ በጎፋ ካፕ ሜዳ የሚገናኙ ይሆናል፡፡

በጉጉት የሚጠበቀውና ጠንካራ ፉክክር የሚያስተናግደው የአንደኛ ዲቪዚዮን የእግር ኳስ የዙር ውድድርም በወሳኝ ምዕራፍ ላይ ይገኛል፡፡ ዘጠኝ ክለቦች ሲፋለሙበት



**የሠራተኛው የበጋ ወራት የእግር ኳስ ውድድሮች በጠንካራ ፉክክር ታጅበው በአጓጊ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ ይገኛሉ፣**

በቆዩት በአንደኛ ዲቪዚዮን ውድድር የተለያዩ ቡድኖች ተቀራራቢ ነጥብ መሰብሰባቸው የፉክክሩን መጨረሻ አጓጊ አድርጎታል፡፡ የውድድር ዓመቱ የዋንጫ አሸናፊ ለመሆን የተለያዩ ቡድኖች እድል ያላቸው ሲሆን በቀጣይ የሚደረጉ ጨዋታዎችም ቻምፒዮኑ የሚለይባቸው ይሆናሉ፡፡

የዋንጫው አሸናፊ ለመሆን የተሻለ እድል የያዙት ኢትዮጵያ ንግድ ባንክና የኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ ተቀራራቢ ነጥብ ይዘው አንድ አንድ ጨዋታ ይቀራቸዋል፡፡ ንግድ ባንክ በ19 ነጥብና 13 ግብ ቀዳሚ ሆኖ ለማጠናቀቅ የቀረውን አንድ ጨዋታ ማሸነፍ ወይ አቻ መውጣት ይጠበቅበታል፡፡ ይህን ጨዋታም ከዮሐንስ ቢፍ ኢን ውሃ ጋር ያደርጋል፡፡ በተመሳሳይ አንድ ጨዋታ እየቀረው በ16 ነጥብና 18 ግብ ሁለተኛ ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች በቀሪው ጨዋታ ኢትዮ ቴሌኮምን ይገጥማል፡፡ ንግድ ባንክ የመጨረሻውን ጨዋታ ተሸንፎ ክፍያ መንገዶች ተጋጣሚውን ማሸነፍ ከቻለ በግብ ክፍያ ስለሚበልጥ ዋንጫውን የማሸነፍ እድል ይኖረዋል። በዚህም ምክንያት ሁለቱ ቡድኖች ከተጋጣሚያቸው ጋር የሚኖራቸው ጨዋታ በጉጉት የሚጠበቅ ሆኗል፡፡

ከእግር ኳስ ባሻገር በሌሎች የስፖርት ዓይነቶች የሚደረጉ ፉክክሮችም ተጠናክረው የቀጠሉ ሲሆን፣ ነገና ከነገ በስቲያም በሁለቱም ፆታ በቮሊቦል፣ ጠረጴዛ ቴኒስ፣ ከረንቦላ፣ ዳርትና ቼዝ ውድድሮች በተለያዩ የማዘውተሪያ ሥፍራዎች ወሳኝ ጨዋታዎች ይካሄዳሉ፡፡

የ2016 የበጋ ወራት ውድድሮች ሰላሳ የሚጠጉ የሠራተኛ ስፖርት ማህበራትን በማሳተፍ "የሠራተኛው ስፖርት ለሰላም፣ ለጤናና ለምርታማነት" በሚል መርህ ባለፉት አራት ወራት ሲካሄድ የቆየ ሲሆን ሰኔ አጋማሽ ይጠናቀቃል ተብሎ እንደሚጠበቅ የኢሠማኮ የስፖርት ክፍል ኃላፊ አቶ ዮሴፍ ካሳ ያደረሱን መረጃ ያመለክታል፡፡ በነዚህ ወራት የውድድሩ ጉዞ የቤት ውስጥ ውድድሮችን ጨምሮ በ10 የስፖርት ዓይነቶች ፉክክር በሚደረግበት የበጋ ወራት ውድድር በሁለቱም ፆታ በአትሌቲክስ፣ ጠረጴዛ ቴኒስ፣ ቮሊቦል፣ ዳማ፣ ቼስ፣ ገበጣ፣ ገመድ ጉተታና ሌሎችም የስፖርት ዓይነቶች ከ1500 በላይ ሠራተኞች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

በዚህ የበጋ ወራት ውድድር የሠራተኞች ስፖርታዊ ተሳትፎ የሚሰሩበትን ተቋም ከማስተዋወቅና የቤተሰባዊ ባለድርሻነት ስሜትን ከማዳበር ባለፈ ጤናማ፣ ንቁና ምርታማ የሚሆኑበት መድረክ ነው፡፡ እነዚህ ውድድሮች ሠራተኞች እርስ በእርስ እንዲተዋወቁ፣ ጤናው የተጠበቀና አምራች ዜጋን ለማፍራት፣ የሠራተኞችን አንድነት ለማጠናከር ፣ የልማት ተቋሞቻቸውን ማስተዋወቀና የባለቤትነት ስሜታቸው እንዲጠናከር አላማ በማድረግ የሚከናወኑ ናቸው። በኢትዮጵያ ረጅም እድሜ ካስቆጠሩ አንጋፋ የስፖርት መድረኮች አንዱ የሆነው ይህ የሠራተኞች ውድድር በዚህ ዘመን ሠራተኛው በስፖርት የሚያደርገው ተሳትፎ ለሚሠራበት ድርጅት ውጤታማነት የሚኖረውን አስተዋጽኦ የጎላ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ስፖርቱ የሠራተኛውን አንድነትና ለጋራ ጉዳይ አብሮ የመቆም ባሕሉን አጠናክሮበታል።

በነዚህ ውድድሮች ላይ ተቋሞቻቸውን ወክለው በሚካፈሉ ተወዳዳሪዎች መካከል ከተቋም ጋር ያለውን መቀራረብ፣ ልምድ ማካፈል እንዲሁም ለተለያዩ ክለቦች ግብዓት የሚሆኑ ስፖርተኞች ማፍራት የቻለ ውድድር መሆኑንም በሠራተኛው ስፖርት ውስጥ ረጅም ዓመታትን ያሳለፉ ሰዎች ይመሰክራሉ። በውድድሩ በሚካፈሉ ተቋማት መካከል በሚፈጠረው ፉክክር ምክንያትም ሠራተኛው የተሻለ ውጤት ይዞ ለመምጣት ሲሽቀዳደምና ለዓመታዊ ውድድሩ ዝግጅት ሲያደርግ መመልከት የተለመደ ነው፡፡

SWEPRS Revenues Bureau
ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል መንግሥት ገቢዎች ቢሮ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

## የባለድርሻ አካላት ቅንጅት - ለሁለንተናዊ የገቢ አስተዳደርና አሰባሰብ

በሀገሪቱ ከመጣው ፖለቲካዊ ለውጥ ጋር ተያይዞ የክልሉ ኢኮኖሚ የሚያመነጨውን ገቢ አሟጦ ለመሰብሰብ በተለይ ባለፉት ሁለት ዓመታት በርካታ ሥራዎች በቅንጅት ሲከናወኑ ቆይተዋል። በዚህም ተጨባጭ ውጤቶች እየተመዘገቡ ቢሆንም፤ በትኩረት ሊሠሩ የሚገቡ ቀሪ የቤት ሥራዎች እንዳሉ መረጃዎች ያመላክታሉ። በክልሉ በተሠራው ሥራ የመጡ ተጨባጭ ውጤቶችን እና ዛሬም ያልተቀረፉ ተግዳሮቶችን ቁልጭ አድርጎ ያሳየ የባለ ድርሻ አካላት የውይይት መድረክ "ቅንጅታዊ ሥራ ለሁለንተናዊ የገቢ አስተዳደርና አሰባሰብ" በሚል መሪ ቃል ከሰሞኑ በሚዛን አማን ከተማ ተካሂዷል። መድረኩ በገቢዎች ሚኒስቴር ጅማ ቅርንጫፍ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል መንግሥት ገቢዎች ቢሮ ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነበር።

በመድረኩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የክልሉ ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሕይወት አሰግድ መንግሥት የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እድገት ለማፋጠን ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለበት ጠቅሰው፤ ይህንን ኃላፊነት ለመወጣት መንግሥት የራሱ ገቢ ያስፈልገዋል። ከዚህ አኳያ የክልሉ ገቢዎች ቢሮ ለአስፈፃሚ አካላት በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት በክልሉ ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በአግባቡ ለመሰብሰብ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

ወይዘሮ ሕይወት፤ አክለውም ክልሉ ሲመሰረት ከነበረበት 2 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር ገቢ የመሰብሰብ አቅም፤ በሁለት ዓመት ውስጥ 6 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ግብ በመጣል ሰፊ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ገልጸው፤ እንደ ክልል ደረሰኝ አለመስጠት፣ ደረሰኝ



**ወይዘሮ ሕይወት አሰግድ፤**

ማበላለጥ፣ ሕገ ወጥ ደረሰኝ መጠቀም፣ ደረሰኝ ያለመቁረጥ ... ወዘተ የገቢ ሕገ-ወጥነት መበራከት መሰብሰብ የሚገባውን ገቢ ለመሰብሰብ ከፍተኛ ተግዳሮት ሆኗል። ስለዚህ በክልሉ እያጋጠሙ ያሉ ሕገ-ወጥነቶችን ለመከላከል እና የሕግ ማስከበር ሥራዎችን ለማጠናከር መድረኩን በልዩ ትኩረት ልናየው ይገባል ብለዋል ኃላፊዋ፡፡

በመድረኩ በግብር ሕግ ማስከበር ዘርፍ ባለፉት ዘጠኝ ወራት የተከናወኑ የአፈፃፀም ሪፖርት ያቀረቡት የክልሉ ገቢዎች ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊና የግብር ሕግ ማስከበር ዘርፍ ኃላፊ ወይዘሮ ትዕግስት በላይ በበኩላቸው በክልሉ ያሉ የግብር ከፋዩ ማህበረሰብ ስለታክስና ቀረጥ አውቆ የንግድ እንቅስቃሴውን እንዲመራ ሰፊ ሥራዎች እየተሠሩ መቆየቱን ገልጸዋል፡፡

ባለፉት ዘጠኝ ወራት በ115 የንግድ ቤቶች ላይ በተደረገ የኦፕሬሽን ሥራ 5 ነጥብ 9 ሚሊዮን ብር የተጭበረበረ ታክስ ገቢ እና በማህደር ምርመራ 2 ነጥብ 1 ሚሊዮን ብር የሚገመት ገቢን ወደ መንግሥት ካዝና ገቢ ማድረግ መቻሉን ወይዘሮ ትዕግስት ባቀረቡት ሪፖርት ጠቅሰው፤ በክልሉ በታክስ ገቢ ማጭበርበር ድርጊት ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ 11 ግብር ከፋዮች በወንጀል ሕግ ተከሰው ጉዳያቸው በምርመራ ሂደት ላይ ይገኛል። እንዲሁም ዘጠኝ የገቢ ተቋማት ባለሙያዎች እጅ ላይ ያለአግባብ ተይዞ የቆየ ከአራት ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ የማስመለስ ሥራ መሠራቱንና ባለሙያዎቹ በመሠወራቸው ከክልሉ ፖሊስ ጋር በመቀናጀት ክትትል እየተደረገ ይገኛል። በመሆኑም የታክስ ስወራና ማጭበርበርን ለመከላከል እንዲሁም ወንጀለኞች ተይዘው ሕግ ፊት ቀርበው ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በቅንጅት እንዲሠሩ በመድረኩ ምክትል ቢሮ ኃላፊዋ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

መድረጉ "ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር ፈተናዎች እና የባለድርሻ አካላት ሚና" በሚል ሁለተኛው የመወያያ ሰነድ በገቢዎች ሚኒስቴር የታክስ ማጭበርበር ምርመራ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ሲሳይ ገዙ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል። አቶ ሲሳይ፤ ታክስ የመሰብሰብ ሥራ በጣም ውስብስብ በመሆኑ የባለድርሻ አካላት ትብብር እና የመረጃ ቅብብሎሽ ሥርዓት ማሻሻል የታክስ ስወራና ማጭበርበርን ለመከላከል ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ ስለዚህ ግብር የሕዝብ ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብ ከታክስ ከሚገኘው ገቢ መንግሥት እና ህብረተሰቡ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የደረሰኝ ሥርዓቱን ወደ ኤሌክትሮኒክስ ኢ-ቮይስ ለመቀየር በፌዴራል ደረጃ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በመድረኩ የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት በበኩላቸው በታክስ ሕግ ማስከበርና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የሚስተዋለውን ችግር ለመፍታት ውይይቱ አስፈላጊና ወቅታዊ መሆኑን አስገንዝበው፤ ገቢን በአግባቡ አለመሰብሰብ የኢኮኖሚ ውድቀት የሚያመጣ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ዘርፉ ብዙ ችግሮችን በማስከተል ሀገር እንደ ሀገር መቀጠል የማይችልበት ሁኔታ ስለሚፈጥር ገቢን በተገቢው መሰብሰብ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

በክልሉ ሁሉን አቀፍ የሆነ ታክስ ስወራ እና ማጭበርበር እኩይ ተግባርን ለመከላከል በየደረጃው የገቢ ተቋማትን በሰው ኃይል፣ በበጀት እና በቁሳቁስ በማጠናከር የአቅም ግንባታ እና የአሠራር ሥርዓት ማበጀት እንደሚገባ በመድረኩ የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት አክለው አንስተዋል።

በመድረኩ ማጠቃለያ ላይ በክልሉ የታክስ ስወራና ማጭበርበር ተግባርን በመከላከሉ ረገድ ወቅቱ የሚጠብቀውን ያህል ባይሆንም ለውጥ እየመጣ መሆኑን የቢሮ ኃላፊዋ ወይዘሮ ሕይወት አሰግድ አመላክተው፤ የታክስ ስወራና ማጭበርበር ችግሮችን በማስወገድ የገቢ አቅምን ለማሳደግና ፍትሃዊ የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን ለማስፈን የታክስ ሕጉ ሳይሸራረፍ ተግባራዊ ለማድረግ በቅንጅት መሥራት እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

በውይይት መድረኩ ላይ ለተነሱ ጉዳዮች ከመድረኩ እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶ ቀጣይ የሥራ አቅጣጫ በማስቀመጥ መድረኩ ተጠናቋል፡፡ በመድረኩ የፌዴራል ገቢዎች ሚኒስቴር ጅማ ቅርንጫፍ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ደሜ ከበደ እንዲሁም የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ጥላሁን ታደመ ጨምሮ ሌሎች የክልልና የዞን ከፍተኛ አመራሮች እና ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል፡፡

ግብር/ታክስ በወቅቱ በመክፈል ወጪዎን ይቀንሱ!
‹‹ስክልላችን ልማት ግብርን በታማኝነት!››
የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል መንግሥት ገቢዎች ቢሮ

በብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ